በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ **1**

መግቢያ **1**

የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት አመሰራረት 1
የድርጅቱ ራዕይና ዓላማ 2
ራዕይ 2
አላማ 2
የቦርዱ ስልጣንና ተግባር 2
የድርጅቱ መዋቅርና የሰው ኃይል 3
ድርጅታዊ መዋቅር 3
የሰው ኃይል 4
የድርጅቱ የፋይናንስ ምንጭ 4
የኦዲቱ ዓላማ 4
ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ 5
የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫዎች 5
የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት 6
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 6
የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዢና ስርጭት አፈፃፀምን የሚመለከቱ የሥራ ሂደቶች መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) 7
የሥራ ቅበላ፣ የምርት አመራረት እና ስርጭት የሥራ ፍሰት 7
በአለም አቀፍ እና በሀገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ለውስጥ ደንበኞች ግዥ መፈፀም 7

ክፍል ሁለት **9**

የኦዲት ግኝቶች **9**

የግዥ ክፍሉ ብቃት ባለው የሰው ኃይል የተደራጀ መሆኑን በተመለከተ፤ 9
ግዢዎች በተዘጋጀላቸው ዕቅድና በጀት መሰረት መፈጸማቸውን በተመለለከተ፤ 9
የግዥ ክፍሉ የግዥ እቅድና ክንውን መረጃ በመያዝ የግዢ ሥርዓቱን መገምገሙን በተመለከተ፤ 10
ጥሬ ዕቃና መሳሪያዎች መሟላታቸውን እና ምርት አለመስተጓጎሉን በተመለከተ፤ 11
ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን (MINIMUM & MAXIMUM STOCK LEVEL) መቀመጡን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ 12
የካፒታል በጀት ግዢ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ መከናወኑን በተመለከተ፤ 13
የግዢ ውሎች ሲዘጋጁ ተፈላጊው መስፈርትና የውል ማጠናቀቂያ ጊዜ በግልጽ መቀመጡን በተመለከተ፤ 14
ድርጅቱ የጥቅል (BULK) ግዢ የሚፈጽም መሆኑን በተመለከተ፤ 15
በግዥ ውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አቅራቢዎች ውል የገቡበትን ዕቃ ገቢ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤ 16
ድርጅቱ ገዝቶ ገቢ ያደረጋቸው ዕቃና መሳሪያዎች በግዢ ትዕዛዙ (SPECIFICATION) መሰረት መሆናቸውን በተመለከተ፤ 17
ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው ገቢ መደረጋቸውን በተመለከተ፤ 18

የትምህርት መሳሪያዎችን ለማምረት፣ ለማሻሻልና ጥራታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል ጥናትና ምርምር መካሄዱን በተመለከተ፤ 19
ድርጅቱ ልዩ ልዩ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቱን በተመለከተ፤ 21
ድርጀቱ የሠራተኞችን ክህሎት በመደበኛ ትምህርትና በስልጠና ማሣደጉን በተመለከተ፤ 22
ድርጅቱ ምርቶችን በተገባው ውለታ መሰረት ለደንበኞች ማስረከቡን በተመለከተ፤ 23
ድርጅቱ ምርቶች በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሰረት ለደንበኞች ማስረከቡን በተመለከተ፤ 24
የድርጅቱ ማሽኖች የሥራ ፍሰታቸውን በመጠበቅ በአንድ ቦታ መተከላቸውን በተመለከተ፤ 25
ድርጅቱ ከትምህርት ዘርፎች ጋር ግንኙነት መፍጠሩን እና ለደንበኞች በሚሰጠው አገልግሎት ግብረ መልስ መሰብሰቡን በተመለከተ፤ 25
ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ፤ 27
ድርጅቱ ምርትና አገልግሎቱን የማስተዋወቅ ሥራ ማከናወኑን እና ውጤቱን መገምገሙን በተመለከተ፤ 28
ድርጅቱ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ 30

ክፍል ሶስት 31

መደምደሚያ 31

ክፍል አራት 34

የማሻሻያ ሀሳቦች 34
አባሪ 1 ድርጅታዊ መዋቅር 38
አባሪ 2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 39
አባሪ 3 በናሙና የታዩ ትምህርት ቢሮዎች፣ ት/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ዝርዝር 42

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. ትምህርት ለምንኖርበት ዓለምም ሆነ ለሰው ልጆች ዕድገትና መሻሻል በር ከፋች ቁልፍ ነው፡፡ በተለይም የትምህርቱ ሂደት ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ ሲሰጥና ሲመራ ጠቀሜታው እጅግ የጎላ ይሆናል፡፡ ሀገራችን በምታስመዘግበው ፈጣን ዕድገት ትምህርት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ መንግስትም ለትምህርት የሰጠው ትኩረት የነገዋ የበለፀገች ኢትዮጵያ የምትደርስበትን የመልካም አስተዳደር፣ ፈጣንና ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህን ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠውን ትምህርት ውጤታማና የታሰበለትን ግብ እንዲያሳካ ከሚያስችሉት አቅጣጫዎች መካከል አንዱ ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ የመማሪያና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችና መጻህፍት በጥራትና በብዛት ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ ይህንን ለማሟላት መንግስት ለኢንዱስትሪው መስፋፋት ያወጣቸውን ፖሊሲዎችና የሚሰጣቸውን ድጋፎች መሰረት አድርገው ከሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች መካከል የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት አንዱ ነው፡፡

የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት አመሰራረት

2. የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት አሁን የሚጠራበትን ስያሜና አደረጃጀት ከማግኘቱ በፊት ለትምህርቱ ሥራ አጋዥ የሆኑ ፅሁፎችና መሳሪያዎች በትምህርት ሚኒስቴር ሥር በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ይዘጋጅ ነበር፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ የትምህርት ፈላጊው ቁጥር እያደገ በዚያው መጠንም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ በ1967 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ሥር በተወሰኑ የፅሁፍ ማባዣ መሳሪያዎች እና በጥቂት ሠራተኞች አዲስ አበባ በሚገኘው በተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ሁለት አነስተኛ ክፍሎች ተሰጥቶት እንደ አንድ የሥራ ዘርፍ ሆኖ ሥራውን ጀመረ፡፡
3. በተለያዩ ክፍሎች በተናጠል የሚከናወኑት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ምርት የትምህርቱ ዘርፍ የሚጠይቀውን ፍላጎት ሊያሟሉ ባለመቻሉ በ1976 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 286/1976 ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ሆኖ ዓመታዊ በጀት ተመድቦለት ራሱን ችሎ ተቋቋመ፡፡ ድርጅቱ በያዘው አቋም ተጠናክሮ ለመማር ማስተማሩ ሥራ የበለጠ አገልግሎት

ሊሰጥ የሚችልበት ደረጃ ለመድረስ እንዲያስችለው በ1991 ዓ.ም በደንብ ቁጥር 50/1991 የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

4. ድርጅቱ እንደ ኢንተርፕራይዝ ሥራ ለመፍጠር፣ የድርጅቱን ዕድገት ለማስመዝገብ፣ ገቢውን ለማሳደግና ትርፍ ለማግኘት የተቋቋመ ሲሆን እንደ መንግስታዊ ተቋምነቱ ደግሞ የትምህርቱን ዘርፍ ዕድገትና ጥራት ለመጠበቅ ዘርፉ የሚገለገልባቸውን የትምህርት መሣሪያዎች በማምረትና በመግዛት አቅርቦቱን የማሟላት ጉልህ ድርሻ አለው፡፡

5. በዚህም መሰረት በዓይነትም ሆነ በብዛት ስፋት ያላቸውን የትምህርት መሳሪያዎች በራሱ በማምረትና ከውጪ ሀገር በማስመጣት ለሀገር ውስጥ ገበያ የማቅረብ ዓላማ ያለው ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ የህትመት ውጤቶችን፣ የጠመኔና ጀሶ ምርቶችን የተለያዩ የትምህርት ቤቶችንና የዩኒቨርስቲዎችን ምርቶች ማለትም ፈርኒቸሮችን፣ መጽሀፎችን፣ የሳይንስ ኪትስ፣ የመሳሰሉትን አምርቶ የሚሸጥና የግዥ አገልግሎት የሚሰጥ የመንግስት የልማት ድርጅት ሲሆን፣ በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በተሰየመ የሥራ አመራር ቦርድ የሚመራ ነው፡፡

የድርጅቱ ራዕይና ዓላማ

ራዕይ

6. "ለአገራችን የትምህርት ሴክተር ለመማሪያና ማስተማሪያ አጋዥ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና የህትመት ውጤቶችን በማምረት ቀዳሚ ተቋም ሆኖ መገኘት"

አላማ

7. በድርጅቱ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 50/1999 መሰረት የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

- ✓ የትምህርት መሳሪያዎችን ማምረት፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ገዝቶ ማቅረብ፣
- ✓ የስልጠናና የሙያ ምክር አገልግሎት መስጠት፣
- ✓ ትርፋማነትን ማሳደግና አስተማማኝ ገበያ መፍጠር እና፣
- ✓ ዓላማዎቹን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ ናቸው፡፡

የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

8. በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት ቦርዱ የሚከተለው ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

- ✓ የፖሊሲ ጉዳዮችን ይወስናል፤
- ✓ የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራል፤ ደመወዝና አበሉን ይወስናል፣ ያሰናብታል፤
- ✓ ለድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር ምደባና ስንብት፣ ደመወዝና አበል ያፀድቃል፤
- ✓ የድርጅቱን የሥራ ፕሮግራም፣ በጀትና የውስጥ ደንብ ያፀድቃል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤
- ✓ የድርጅቱን የረጅም ጊዜ ብድሮችና ክሬዲቶች ያፀድቃል፤
- ✓ በድርጅቱ ሕልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያፀድቃል፤
- ✓ የድርጅቶቹ ሂሳቦችና ንብረቶች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤
- ✓ ለድርጅቱ ኦዲተሮች የድርጅቱን የሂሳብ መዝገቦች፣ ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን ደግሞ ስለድርጅቱ የሥራ አፈፃፀም ወቅታዊ ሪፖርትና የሂሳብ መግለጫዎች ያቀርባል፤
- ✓ የድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን ሃሳብ ያቀርባል፡፡

የድርጅቱ መዋቅርና የሰው ኃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

9. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 50/1991 መሰረት የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ተጠሪነቱ በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ለተሾመ ሥራ አመራር ቦርድ ሲሆን፣ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለኤጀንሲው ነው፡፡ ድርጅቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተርና በአንድ ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን፣ በዋና ዳይሬክተሩ ስር የህግ አገልግሎት፣ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት፣ የጥራት ምርምርና ስርፀት አገልግሎት፣ የሰው ሀብት ሥራ አመራርና የተቋማዊ ለውጥ ዳይሬክቶሬት፣ የዕቅድ ገበያ ልማትና መረጃ ዳይሬክቶሬት እና የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት የሚገኙ ሲሆን፣ በምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ስር ደግሞ የአቅርቦትና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የመሳሪያዎች ጥገናና ኢንጂነሪንግ ዳይሬክቶሬት፣ የአታሚና አሳታሚ ዳይሬክቶሬት እና የፈርኒቸር የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማምረቻ ዳይሬክቶሬት ይገኛሉ፡፡ የድርጅቱ መዋቅር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

የሰው ኃይል

10. የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በህዳር ወር 2006 ዓ.ም 217 (44%) ሴት ሰራተኞች 279 (56%) ወንድ ሰራተኞች በድምሩ 496 የኮንትራትና ቋሚ ሰራተኞች ያሉት ሲሆን፣ ከነዚህ በተጨማሪም 235 ጊዜያዊ ሰራተኞች አሉት፡፡ ድርጅቱ ያለው የሰው ኃይል በሙያ ሲተነተን ኘሮፌሽናል 43 (9%)፣ መለስተኛ ኘሮፌሽናል 44 (9%)፣ የቴክኒክና ሙያ 137 (28%) እና ከዛ በታች ያሉ 272 (55%) መሆናቸው ታውቋል፡፡

የድርጅቱ የፋይናንስ ምንጭ

11. የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የፋይናንስ ምንጭ ከትምህርት መሳሪያዎች ሽያጭ ገቢ፣ ከግዥ አገልግሎት ገቢ ማለትም ድርጅቱ ለውጭ ደንበኞች የግዥ አገልግሎት ሰጥቶ ከሚያገኘው የአገልግሎት ክፍያ እና ከባንክ ብድር ሲሆን፣ ከ2003-2005 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ካፒታል የተመደበው በጀት እና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

በጀት ዓመት		ተፈቀደ በጀት (በብር)	ስራ ላይ የዋለ በጀት (በብር)	ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ
2003	መደበኛ	85,145,999.00	66,316,815.00	78%
	ካፒታል	8,276,000.00	6,056,000.00	73%
2004	መደበኛ	96,614,234.00	136,540,693.00	141%
	ካፒታል	16,050,000.00	16,050,000.00	100%
2005	መደበኛ	122,102,984.00	151,643,557.00	124%
	ካፒታል	10,150,000.00	10,150,000.00	100%

የኦዲቱ ዓላማ

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን እንዲሁም ከሀገሪቱ የትምህርት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ እና መሰረታዊ የትምህርት መስፋፋት ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እንዲሆን እና ድርጅቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር እገዛ የሚያደርግ መሆኑን መገምገም

ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

13. ለዝርዝር ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ ትኩረት አቅጣጫዎች

14. ከላይ ለተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና አራት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡ እነርሱም፥
    1. በድርጅቱ የተፈፀሙት የትምህርት መሳሪያዎች ግዥ የመንግስትን የግዥ ሥርዓት ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን እና በወቅቱ ለተጠቃሚው ክፍል የተሰራጨ መሆኑን ማረጋገጥ፤
        - 1.1. የድርጅቱ የግዥ ሂደት የመንግስትን የግዥ ደንብ እና መመሪያ ተከትሎ ተፈፀመ መሆኑን መገምገም፣
        - 1.2. በድርጅቱ የተፈፀሙ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥና ስርጭት በውሉ መሰረት መፈፀማቸውን በወቅቱ ለተጠቃሚው ክፍል መሰራጨታቸውን መገምገም፣
    2. ድርጅቱ ተጠቃሚው የሚፈልገውን ምርት በመጠን፣ በአይነትና በጥራት በሚፈለገው ጊዜና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያቀርብበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤
    3. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎች ግዢና ስርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓትን የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን እና ቀልጣፋ ኢኮኖሚያዊ እና ብቃት ያለው የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን መገምገም፤
        - 3.1. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎች ግዢና ስርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓትን ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤

3.2. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት በተመለከተ የሚያደርገው የመረጃ ልውውጥና የማስተዋወቅ ሥርዓት ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊና ብቃት ያለው መሆኑን መገምገም፤

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት

15. ከላይ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና አራት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 38 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ድርጅቱ የተቋቋመበት የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ፣ የድርጅቱ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ እና አመታዊ ዕቅድ፣ የድርጅቱ የግዥ መመሪያዎች፣ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናቶች እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ ድርጅቱ በመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ተደርጎ የተስማማ መሆኑን ገልጿል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

16. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2003-2005 ያሉትን የአራት በጀት ዓመታት እና የ2006 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡
17. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ዋና መ/ቤት፣ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ሽሮ ሜዳ ቅርንጫፍ፣ እንዲሁም በናሙና በተመረጡ በአዲስ አበባ እና በክልል በሚገኙ ትምህርት ቢሮዎች፣ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርስቲዎች እንዲሁም በድርጅቱ ሥር ከሚገኙ የሽያጭ ጣቢያዎች በመገኘት ለሚመለከታቸው ሰራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት ጋር ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን በመከለስ እንዲሁም በአካል ተገኝቶ በማየት ነው፡፡
18. ከዚህም በተጨማሪ በናሙና በመስክ ሥራ ላልተሸፈኑት ትምህርት ቢሮዎች፣ ትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች መጠይቆች (Survey questionnaires) በመላክ መረጃዎች

ተሰብስበዋል፡፡ (በናሙና ተመርጠው የታዩ ትምህርት ቢሮዎች፣ ት/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡)

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዢና ስርጭት አፈፃፀምን የሚመለከቱ የሥራ ሂደቶች መግለጫ (Process Description)

የሥራ ቅበላ፣ የምርት አመራረት እና ስርጭት የሥራ ፍሰት

19. ደንበኛው የምርት ናሙና ወይም ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን ይዞ ይቀርባል ወይም የድርጅቱን ስታንዳርድ ምርቶች ያዛል፡፡ የጥሬ ዕቃና ምርቱን ለማምረት የሚፈጀው ጊዜ ተተምኖ የማምረቻ ዋጋና የትርፍ ህዳግ ተዘጋጅቶ ለደንበኛው ይገለፃል፡፡ የደንበኛው ምላሽ አሉታዊ ከሆነ ያቀረባቸው ናሙናዎች ተመላሽ የሚሆኑ ሲሆን፣ ደንበኛው አዎንታዊ ምላሽ ከሰጠ ግን ውል ተዘጋጅቶ ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል፡፡ በመቀጠል ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን በማዘጋጀት ከውለታው ጋር በደብዳቤ ለምርት ይተላለፋል፡፡ በመጨረሻ የተመረተው ምርት ወደ ግምጃ ቤት በምርት ማስተላለፊያ ሰነድ ገቢ ከሆነ በኋላ ከግምጃ ቤት በዱቤ ወይም በቀጥታ ሽያጭ ለደንበኛው ይሰጣል፡፡

በአለም አቀፍ እና በሀገር ውስጥ ግልፅ ጨረታ ለውስጥ ደንበኞች ግዥ መፈፀም

20. በአለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ለደንበኞች ግዥ ለመፈፀም በመጀመሪያ የተሟላ ስፔስፊኬሽን ከውስጥ ደንበኞች በመቀበልና ከደንበኛው የቀረበውን ስፔስፊኬሽን በመገምገም የጨረታ ሰነድ ተዘጋጅቶ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል፡፡ በመቀጠል የጨረታ ሰነድ በመሸጥ ጨረታ ሰነዱን ግልፅ በሆነ መንገድ የመክፈትና የመዝጋት ሥራ ይሰራል፡፡ የግዥ ቡድኑ የቴክኒክና የፋይናንሻል ግምገማ በማካሄድ አሸናፊውን በመለየት ቃለ ጉባዔ በማዘጋጀት የማፅደቅ ሥራ ያከናውናል፡፡
21. የግዥ ክፍሉ የግዥ ትዕዛዝ በመስጠት የኮንትራት ውል በማዘጋጀት ከአቅራቢዎች ጋር ውል በመፈራረምና ለተወዳዳሪዎች ውጤቱን በማሳወቅ በጨረታው ላላሸነፉ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ማስከበሪያ ይመለስላቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በግዥ ክፍሉ አማካኝነት ለተገዙት ዕቃዎች ኢንሹራንስ መግባት፣ የውጭ ምንዛሪ መጠየቅ፣ የጨረታ ሰነድ መረከብና የክሊራንስና የማጓጓዣ ሥራ ከተካሄደ በኋላ ክፍያ ማዘጋጀት ለአቅራቢዎች መላክ

ቀጥሎም ዕቃውን ማስፈተሽና ጥራቱን በደንበኛው በማረጋገጥ ለደንበኛው ማስረከብ ይሆናል፡፡

22. ደንበኞች ከተረከቡ በኂላ እንደ ዕቃው አይነት የተከላና የስልጠና ሥራ እንዲከናወን በማድረግ ቀሪ ክፍያ ካለም ለአቅራቢው እንዲከፈል ይደረጋል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ግዥ ከሆነ ድርጅቱ ለሚያደርገው የግዥ አገልግሎት ክፍያ ገቢ እንዲያደርግ ለደንበኛው የማሳወቅ ሥራ ይሰራል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

የግዥ ክፍሉ ብቃት ባለው የሰው ኃይል የተደራጀ መሆኑን በተመለከተ፤

23. የግዥ ክፍሉ በሚገባ ሊደራጅና ብቃት ባለው የሰው ኃይል ሊሟላ ይገባል፡፡
24. በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ የግዥ ክፍል በሥራ ላይ ያሉ 11 ሰራተኞች የግል ማህደር ሲከለስ 6ቱ በሥራ መደቦች የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛ መስፈርት መሰረት የሚፈለገውን ተፈላጊ ችሎታ ያላሟሉና ቦታው የሚጠይቀው የኮምፒውተር ዕውቀት የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
25. ስለሁኔታው የድርጅቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ቢጠይቅም በሂደት ለማሟላትና ማህበራዊ ቀውስ በማያስከትል ሁኔታ ነባሮቹንና ልምድ ያላቸውን በማሸጋሸግ ለመመደብ እየተሞከረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
26. የግዢ ክፍሉ ብቃት ባለው የሰው ሀይል የተደራጀ አለመሆን የግዥ ሥራው የተቀላጠፈ እንዳይሆንና የግዥ ሂደቱ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ እንዳይከናወን አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ግዢዎች በተዘጋጀላቸው ዕቅድና በጀት መሰረት መፈጸማቸውን በተመለለከተ፤

27. የድርጅቱ ግዥዎች በቅድሚያ በተዘጋጀላቸው ዕቅድና በጀት መሰረት መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡
28. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው፤ በ2003 በጀት አመት የብር 2,637,000 የኬሚካልና የአፓራተስ የግዥ አገልግሎት በመስጠት ብር 6,590,000 ገቢ ለማግኘት በጀት የተያዘና የታቀደ ቢሆንም አለመከናወኑን፣ በ2005 የዘጠኝ ወር የሥራ አፈፃፀም የውጭ ሀገር ግዥ ብር 21,702,000 ለመፈጸም ታቅዶ ምንም አለመከናወኑን፣ በተጨማሪም በዚሁ በ2005 በጀት አመት ከኬሚካልና ከአፓራተስ ግዥ ብር 4,000,000 ገቢ ለማግኘት ታቀዶ ብር 885,000 ወይም (22%) ብቻ የተገኘ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
29. ስለሁኔታው የድርጅቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት፤ ሥራን አቅዶ ያለመስራት የአቅም ውስንነት መኖሩንና ይህን ለማሻሻል በአደረጃጀት ማሻሻያ እየተደረገ መሆኑን፣ ድርጅቱ በራሱ ገቢና በባንክ ብድር የሚንቀሳቀስ

ስለሆነ የታቀደውን መፈፀም ቢኖርበትም በገንዘብ እጥረት፣ የዕቃው ዋጋ አዋጭ ባለመሆኑና ውድ በመሆኑ ወዘተ… በታሰበው መጠን ግዥ ለመፈፀም አለመቻሉን፣ አንዳንድ ግዥዎች ምንም እንኳን በ2005 በጀት አመት ሊገዙ ቢታቀዱም በውጭ ምንዛሪ ችግርና ደንበኞች ገንዘብ ገቢ ባለማድረጋቸው ዘግይቶ በ2006 በጀት ዓመት የሚገዛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

30. ግዥዎች በቅድሚያ በተዘጋጀላቸው ዕቅድና በጀት አለመፈፀማቸው ጥቃቅን ግዥዎች በተደጋጋሚ እንዲፈጸሙ ከማድረጉም በላይ የድርጅቱ የሥራ አፈፃፀምና እንቅስቃሴ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድርጅቱ በኬሚካልና አፓራተስ የግዢ አገልግሎት ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዳያገኝ እና በትምህርት ቤቶች የተግባር ትምህርት እንዲደናቀፍ ያደርጋል፡፡

የግዥ ክፍሉ የግዥ እቅድና ክንውን መረጃ በመያዝ የግዢ ሥርዓቱን መገምገሙን በተመለከተ፤

31. የግዥ ክፍሉ በየጊዜው የሚያዘጋጀውን የግዥ እቅድና ክንውን የተጠናከረ ማስረጃ በመያዝ የግዢ ሥርዓቱን መገምገም እና ፈጣን ማድረግ ይኖርበታል፡፡
32. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ የግዢ ሥርዓቱን በመገምገም ፈጣን ለማድረግ የተሰራውን ሥራ የሚያመለክቱ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ሊያቀርብ አልቻለም፡፡
33. የድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች ማስረጃዎቹ ሊቀርቡ ያልቻሉበትን ምክንያት እንዲገልጹ ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት የግዥ ክፍሉ በአግባቡ ካለመደራጀቱም በላይ በሰው ኃይልና በአሠራር የተጠናከረ አለመሆኑን፣ ይህን ለማስተካከል በአሁኑ ወቅት የአቅርቦትና ንብረት አስተዳደር ተቋቁሞ ሥራዎች በአግባቡ እንዲሰሩ እየተሞከረ መሆኑን እና ከዚህ ውጪ የግዥ ሥራ በሳምንት፣ በወርና በየሩብ አመቱ ከድርጅቱ አፈፃፀም ጋር በማኔጅመንትና በቦርድ እንደሚገመገምና በቀጣይ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡
34. የግዥ ክፍሉ በየጊዜው የሚያዘጋጀውን የግዢ እቅድና ክንውን ማስረጃ በተደራጀ መልኩ ካልያዘና የግዢ ሥርዓቱን በየጊዜው በመገምገም ፈጣን እንዲሆን ካላደረገ የግዢ አፈጻጸሙ ቀልጣፋና ዘመናዊ እንዳይሆንና በግዢ ሂደቱ ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሻሉ አሰራሮችን ለመዘርጋት እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

ጥሬ ዕቃና መሳሪያዎች መሟላታቸውን እና ምርት አለመስተጓጎሉን በተመለከተ፤

35. የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊ በሆኑ ጥሬ ዕቃና መሳሪያዎች መሟላት አለበት፡፡

36. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፤

- ✓ አንድ ምርት ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ በጥሬ ዕቃ እጥረት ምክንያት የሚቆም እና ምርቱ ከቆመ በኋላ የግዥ ጥያቄ የሚቅርብ መሆኑን፣
- ✓ ሥራን በዝርዝር ቆጥሮ የመስጠትና ቆጥሮ የመቀበል የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ አለመቅረቡን፣
- ✓ በ2004 ዓ.ም ምርት ላይ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት እጥረት በማጋጠሙ የተማሪዎች መኘታ ቤት ጠረጴዛ የብረት ሥራው ተሰርቶ የእንጨት ሥራውን ለማምረት የፎርማይካ አቅርቦት ችግር ያጋጠመመበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ✓ ድርጅቱ የሚያስፈልጉትን መለዋወጫ ዕቃዎች አስቀድሞ በመለየት በወቅቱ ግዥ ባለመፈጸሙ የማምረቻ ማሽኖች የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ✓ በጠመኔ ማምረቻ ክፍል ውስጥ የማድረቂያ በርነሮች በእርጅና ምክንያት ተደጋጋሚ ብልሽት ያጋጠማቸው በመሆኑ የክፍሉን ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ዝቅ ያደረገው መሆኑን፣
- ✓ ሽት ፊድ (ዝርግ ወረቀቶችን የሚያትሙ) የህትመት መሳሪያዎች ብልሽት አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱ እና ከፍተኛ የሆነ የወረቀት አቅርቦት ዕጥረት በተደጋጋሚ ማጋጠሙን፣
- ✓ በ2005 ዓ.ም በድርጅቱ በሥራ ላይ የሚገኙት የእጅ መብሻ ማሽኖች /Hand drilling Machine/ ግማሾቹ በተለያየ ጊዜ ቢጠገኑም ተመልሰው ወደ ሥራ መግባት የማይችሉበት ደረጃ ላይ የደረሱ መሆኑ እና ቀሪዎቹ በተደጋጋሚ በመበላሸት የማምረት ሂደቱ ላይ ተፅዕኖ እያሳደሩ መሆኑን፣

ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

37. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት፡-

- ✓ ሥራ በዝርዝር ቆጥሮ የመስጠትና የመቀበል ሥርዓትን ለመተግበር ጥረት እየተደረገ እንደሆነና የበለጠ መሻሻል የሚገባ መሆኑን፣

- ✓ ማሽኖች በከፍተኛ ደረጃ ያረጁና መተካት የሚገባቸው እንደሆኑ ነገር ግን የገንዘብ እጥረት ስላለ በሚፈለገው መጠን መተካት ባይቻልም ያሉትን በመጠገንና በመንከባከብ የሚፈለገውን ምርት ለማምረት መቻሉን፣
- ✓ የጠመኔ ማምረቻው ማሽን በጣም ያረጀና ከገበያ ውጭ በመሆኑ መለዋወጫ እንዳልተገኘለትና በውስጥ አቅም ሞዲፋይ በማድረግ (በማስተካከል) በሚቻለው አቅም ለማምረት እየተሞከረ መሆኑን፣
- ✓ ከጥገና፣ ከማሽን እንክብካቤ፣ ከብክነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የካይዘን አሰራር በመተግበር ላይ መሆናቸውን፣
- ✓ የመለዋወጫ ፍላጎትን በተመለከተ ሁሉንም ገዝቶ ማስቀመጥ የሚያዳግት ቢሆንም የተወሰነ መጠን ተገዝቶ እንደሚቀመጥና አንዳንድ ጊዜ በክምችት የሌለ መለዋወጫ ማሽኑ ላይ ሲበላሽ የሚገጥመውን ችግር ለመቅረፍ ሲባል በሚቻለው አማራጭ ግዥ እንደሚፈፀም ገልጸዋል።

38. በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ማሽኖች ረጅም ጊዜ ያገለገሉና በተደጋጋሚ ብልሽት የሚገጥማቸው በመሆኑ በምርት ሥራው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማለትም የብክነት መጠንን የመጨመር፣ የምርት ጥራትን የመቀነስ፣ እንዲሁም የማስረከቢያ ጊዜን የማራዘምና የጥገና ወጪን የመጨመር ችግር ያስከትላሉ። እንዲሁም የማሽን መለዋወጫ እጥረት በመኖሩ ማሽኖቹ በትክክል የሚፈለገውን ምርት ሊያመርቱ ካለመቻላቸውም በላይ የምርት መቀነስ፣ የሠራተኞች ያለስራ መቀመጥ፣ የደንበኛ ምልልስ አጠቃላይ የስራ መስተጓጎልን ያስከትላል።

ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን (minimum & maximum stock level) መቀመጡን እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

39. በድርጅቱ አላስፈላጊ ክምችት እንዳይያዝ ወይም በቂ ክምችት ባለመኖሩ እጥረት እንዳይፈጠር በጥናት ላይ ተመስርቶ በየዕቃዎቹ ዓይነት ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን (minimum & maximum stock level) ሊቀመጥና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።
40. ይሁን እንጂ ጥናት ተደርጎ በየዕቃዎቹ አይነት ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን ተቀምጦ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል። በዚህም ምክንያት በ2006 በጀት አመት ድርጅቱ በቂ የጥሬ ዕቃና የመለዋወጫ ዕቃዎች ክምችት ባለመያዙ በርካታ ስራዎችን ተወዳድሮ መውሰድ እንዳልቻለ፣ የሥራ ዘርፎች የግዥ

ጥያቄ የሚያቀርቡት በክምችት ያለው ዕቃ ሙሉ በሙሉ ካለቀ በኋላ በመሆኑ ሥራ እንዳይቆም ግዢ በአስቸኳይ የሚጠየቅ በመሆኑ በጨረታ መገዛት ያለባቸው ግዢዎችም በፕሮፎርማ እንዲገዙ መደረጉን፣ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. በተጨማሪም ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 622,350.55 የሆኑ 12 ዓይነት ጅግ (የሳይንስ ኪት ማምረቻ ማሽን) እንዲሁም ሀይ ዴንሲቲ ፐሊተሊኒግ ለሳይንስ ኪት መስሪያ የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎች ከ2001 ጀምሮ ከአምስት ዓመት በላይ በዕቃ ግምጃ ቤት ያለ አገልግሎት መቀመጣቸውን ከ2004 በጀት የ4ኛ ሩብ አመት የውስጥ ኦዲት ሪፖርት እና በአካል በመገኘት ለማየት ተችሏል፡፡

42. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት የክምችት መጠኑን እየጠበቁ ሁሉንም ዓይነት መለዋወጫ መግዛት በገንዘብ እጥረትና በአቅም ውስንነት ምክንያት እንዳልተቻለ፣ ተገዝተው ሲቆዩ የመበላሸት ሁኔታም እየተከሰተ መሆኑን፤ ወረቀትን በተመለከተ በአገር ውስጥ በአንሞል የወረቀት ማምረቻ ብቻ ስለሚመረትና እንደየፍላጎታቸው በየወቅቱ እንደሚገዙ፤ ለሳይንስ ኪት ማምረቻ የሚያገለግለውን ጥሬ ዕቃ በተመለከተ በአሁኑ ወቅት የፕላስቲክ ማምረቻ ማሽን መግዛትና ማምረት ከአቅም አንጻር አዳጋች እንደሆነና ቀደም ሲል የተገዙ ጥሬ ዕቃዎችን ግን በማጣራት ሳይበላሹ በሽያጭ ማስወገድ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

43. ድርጅቱ ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የክምችት መጠን አስቀምጦ ተግባራዊ ባለማድረጉ ለምርቱ ሂደት በቂ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ክምችት እንዳይኖር በማድረግ በደንበኞች የሚታዘዘውን ምርት በወቅቱ አምርቶ ለማስረከብ እንዳይቻል የሚያደርግ ሲሆን፣ የጥሬ ዕቃ ግዢ አፈፃፀም በፕሮፎርማና በውሱን ጨረታ የግዢ ስልት ብቻ ተወስኖ በየጊዜው የተቆራረጠ ግዥ እንዲፈጸም በማድረግ እንዲከናወንና የማምረቻ ዋጋ (production cost) እንዲጨምር እንዲሁም የጥሬ ዕቃ ብክነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

የካፒታል በጀት ግዢ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ መከናወኑን በተመለከተ፤

44. የካፒታል በጀት ግዢ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መከናወን ይገባዋል፡፡

45. የካፒታል በጀት ግዢ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑ በሚጣራበት ወቅት፡-

- ✓ በ2003 በጀት አመት ለማምረቻ ማሽኖች፣ ለቢሮ ዕቃዎች፣ ለህንፃ ግንባታ፣ ለተሽከርካሪዎችና ለጥናቶች ማካሄጃ ብር 8,276,000 የተፈቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለድርጅቱ የመረጃ መረብ ዝርጋታ የሚውሉ ዕቃዎች የተገዛበት ብር 1,162,000 (14%) መሆኑ እና ዝቅተኛ አፈፃፀም ያለው መሆኑን፣
- ✓ በ2004 በጀት ዓመት ለማምረቻ ማሽኖች ብር 16,050,000 በጀት ተይዞ perfect binding & Auto side stitching machine ግዢ ለመፈጸም ጨረታ ወጥቶ ከተገመገመ በኋላ ዋጋው በመወደዱ ጨረታው እንዲሰረዝ ሲደረግ ሌላ አማራጭ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑን፣
- ✓ በ2005 በጀት ዓመት የወረቀት መስፊያ ማሽን ግዢ ለመፈጸም ብር 2 ሚሊየን በጀት ተይዞ ጨረታ ወጥቶ የተመረጠው ማሽን ከብር 4 ሚሊየን በላይ የሚጠይቅ ሆኖ በመገኘቱ ከድርጅቱ አቅም አንፃር ግዥውን መሰረዝ አግባብ መሆኑ ስለታመነበት በሚል ግዥው ያልተፈፀመ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል።

46. ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫው ላይ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት አስተያየት ድርጅቱ የሚንቀሳቀሰው ከባንክ በሚያገኘው ብድር በየወቅቱ የብድር ክፍያውንና ወለዱን በመክፈል መሆኑን፣ ከዚያ ውጭ የሚመደብለት በጀት እንደሌለ፣ ከባንክ የሚገኘውም ብድርም የተወሰነ ብቻ በመሆኑ በየወቅቱ ሊገዙ የሚታሰቡ የካፒታል ፕሮጀክት ግዥዎች በዋናነት በገንዘብ እጥረት የማይፈጸሙበት ሁኔታ መከሰቱ እንደማይቀርና በቀጣይ የገንዘብ አቅም የሚፈቅድ ከሆነ እንደገና ታቅዶ ለመግዛት እንደሚሞከር ገልፀዋል።
47. የካፒታል በጀት ግዢ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ መሰረት አለመፈጸሙ ድርጅቱ ሥራውን በዕቅዱ መሰረት እንዳያከናውን ያደርጋል።

የግዢ ውሎች ሲዘጋጁ ተፈላጊው መስፈርትና የውል ማጠናቀቂያ ጊዜ በግልጽ መቀመጡን በተመለከተ፤

48. የግዢ ውሎች ሲዘጋጁ ተፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ፣ ለአገልግሎትም ሆነ ለእቃ ግዢ ተፈላጊው መስፈርትና የውል ማጠናቀቂያ ጊዜው በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል።
49. በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ የተፈራረማቸው የግዢ ውሎች ሲታዩ ከድሬዳዋ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጋር የተፈረሙ ሁለት ውሎች ውሉ የተፈረመበት እና ውሉ የሚጠናቀቅበት ጊዜ በውሉ ላይ ያልተገለጸ መሆኑን፣ ከአንሞል ኢትዮጵያ

ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር የተፈፀመው ውል ውሉ የሚጠናቀቅበት ቀን ያልተገለጸ መሆኑን እና ከዚሁ የወረቀት አቅራቢ ድርጅት ጋር በ2003 ዓ.ም በተደረገ ውል የውል ማጠናቀቂያው እና ውል የተፈፀመበት ቀን ያልተጠቀሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

50. ስለሁኔታው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ የድርጅቱ ኃላፊዎች በሰጡት አስተያየት ውል በሁለት ወገኖች የሚፈፀም እንደመሆኑ መጠን ውል ሰጪ በመስማማቱና ድርጅታቸውን ስለሚጠቅም የተቀበሉት እንደሆነና በቀጣይም እንደግብዓት እንደሚወስዱት ገልፀው፣ የወረቀት ግዥን በተመለከተም ወረቀት የሚያመርተው አንሞል ብቻ በመሆኑና እንደልብ ምርቱ የማይገኝ በመሆኑ ከሥር ከሥር ለመረከብና በተረከቡት መጠን ለመክፈል ታስቦ የተገባ ውል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

51. የግዥ ውሎች የተፈፀሙበትና የሚጠናቀቁበት ጊዜ በግልፅ ካልተቀመጠ አቅራቢውን የሚያስገድድ ህግ ባለመኖሩ አቅራቢው ወቅቱን ጠብቆ የሚፈለገውን ዕቃ የሚያቀርብበት ሁኔታ እንዳይኖር ያደርጋል፡፡፡ ጥሬ ዕቃ በወቅቱ አለመድረሱ ደግሞ በደንበኞች የታዘዘው ምርት በወቅቱ እንዳይደርስ እንቅፋት ይሆናል፡፡

ድርጅቱ የጥቅል (bulk) ግዢ የሚፈጽም መሆኑን በተመለከተ፤

52. ድርጅቱ በጥቅል መገዛት ያለባቸውን የዕቃዎች እና የአገልግሎት ግዥዎች በጥቅል (bulk) መፈጸም አለበት፡፡

53. በኦዲቱ ወቅት የድርጅቱ የተለያዩ የግዢ ማስረጃዎች ሲከለሱ የአልሚኒየም ሽት ሜታል፣ ፓይነስ ጣውላ፣ ስኩየር ፓይፕ፣ ነጭ ፎርማይካ፣ ጣውላ፣ ቪናቪን ኮላ፣ ለማተሚያ ቤት የሚውል ጥቁር ቀለም፣ ለህትመት የፕሮሰስ ቢጫ ቀለም፣ ለማተሚያ አርት ፔፐር እና የመሳሰሉት በቁጥ ቁጥ ግዥ በተደጋጋሚ እንደተገዙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

54. ከዚህም በተጨማሪ የሀገር ውስጥ አብዛኞቹ ግዥዎች የተከናወኑት በፕሮፎርማ /በቁጥቁጥ/ ግዥ መሆኑን፣ በ2005 በጀት አመት አብዛኛው የፈርኒቸር ምርት ጥሬ ዕቃ ግዥ በግልፅ ጨረታ አለመገዛቱ ከ2002 ሶስተኛ ሩብ ዓመት እና ከ2005 ሁለተኛ ሩብ አመት የውስጥ ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የጥሬ ዕቃ ክምችት ሲያልቅ የግዥ ጥያቄ ከአምራች ክፍል የሚቀርብ በመሆኑ መሆኑን ከመረጃው ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. ከዚህም በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ግዥን በተመለከተ ከቀረበ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ከፍተኛ ዋጋ ያለው ጣውላ፣ ፕላይ ውድ፣ ሽት ሜታል ከተወሰኑ አቅራቢዎች በተደጋጋሚ በውስን ጨረታ መገዛቱን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

56. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ የጥሬ ዕቃ በጥቅል የሚገዛባቸው ሁኔታዎች በርካታ መሆናቸውን፣ አልፎ አልፎ የጥቅል ግዥ የማይፈፀመው ጥሬ ዕቃ ግዥውም ሆነ ምርቱ የሚከናወነው ትዕዛዝ ሲመጣና እንደሚመረተው የምርት አይነት መሆኑን፣ በገንዘብ እጥረት ያለአግባብ ገንዘብ በክምችት ላይ እንዳይያዝ በመስጋት እና አስቀድሞ የሚሸጠውንና የሚመረተውን በአግባቡ ገምቶ በዚያው መጠን በብዛት የመግዛት አቅም ሲያንስ እንደሆነና በቀጣይ ሁኔታዎቹን እንደአግባቡ በመመዘን በብዛት መግዛት የሚገባቸውን ዕቃዎች በብዛት ለመግዛት እንደሚሞከር ገልጸዋል፡፡

57. በክምችት ላይ የሚውል ገንዘብን ለመቀነስ ሲባል ጥሬ ዕቃ በቁጥ ቁጥ መግዛት የምርት ክፍል ቅልጥፍናን የሚያሳጣና የደንበኞችን ፍላጎት የማያሟላ ከመሆኑ በላይ የመግዣው ዋጋ ከፍተኛ ስለሚሆን የመወዳደር አቅምና ትርፋማነት የሚቀንስበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በተጨማሪም ድርጅቱ ግዢዎችን በጥቅል ባለመግዛቱ ምርቱ በሚፈለገው መጠን እንዳይመረትና ድርጅቱ አቅሙን መጠቀም እንዳይችል ያደርገዋል፡፡

በግዥ ውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አቅራቢዎች ውል የገቡበትን ዕቃ ገቢ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤

58. በግዥ ውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃ አቅራቢዎች ውል የገቡበትን ዕቃ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት በድርጅቱ ለሚመረቱ ፈርኒቸሮች አገልግሎት የሚውል 4,000 ሀርድ ቦርድ ከኢትሀርሶ ለመግዛት ስምምነት ተደርጎ 1,700 ገቢ ሲደረግ ቀሪው 2,300 ገቢ ባለመደረጉ በምርቱ ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳስከተለ የግዥ ቡድን መሪ በቁጥር 7/2666/9/02 ለኢትሀርሶ ከፃፈው ደብዳቤ ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ድርጅቱ ለመማሪያ መጻህፍት ህትመት የሚውል ወረቀት ከአንሞል ወረቀት አምራች የሚገዛ ሲሆን የወረቀት አምራቹ የሚፈለገውን የወረቀት መጠን በሚፈለገው ጊዜ ለማቅረብ ባለመቻሉ በሥራ ላይ ችግር እንዳስከተለ ለዋና ዳይሬክተሩ ከአታሚና አሳታሚ ዳይሬክቶሬት ከተፃፈ ደብዳቤ ለመረዳት ተችሏል፡፡

60. ይህንንም በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ የድርጅቱ ኃላፊዎች በሰጡት አስተያየት ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገዙ ዕቃዎች አልፎ አልፎ የሚዘገዩበት ሁኔታ በመኖሩ ችግሩን ከአቅራቢዎች ጋር ለመፍታት እየተሞከረ መሆኑን፣ ወረቀትን የመሳሰሉ ሌሎች ዕቃዎች ግን ከሌላ አማራጭ መግዛት ስለማይቻል ሥራ የሚቆምበት ሁኔታ መኖሩን፣ ይህን ችግር ለመቅረፍ ባላቸው ውሱን የገንዘብ አቅም ከውጭ 1000 ቶን ጥቅል ወረቀት ለመግዛት በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

61. ዕቃ አቅራቢዎች በግዥ ውሉ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውል የገቡበትን ዕቃ ማቅረብ ካልቻሉ ድርጅቱ በሚያመርተው ምርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ምርቱ ለደንበኞች በወቅቱ እንዳይርሳቸው እና ደንበኞች ድርጅቱ በሚሰጠው አገልግሎት እርካታ እንዲያጡ ያደርጋል፡፡

ድርጅቱ ገዝቶ ገቢ ያደረጋቸው ዕቃና መሳሪያዎች በግዢ ትዕዛዙ (Specification) መሰረት መሆናቸውን በተመለከተ፤

62. ድርጅቱ ገዝቶ ገቢ ያደረጋቸው ዕቃና መሳሪያዎች በግዢ ትዕዛዙ (Specification) መሰረት መሆናቸው በቅድሚያ በሚመለከተው አካል (ባለሙያ) ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

63. በኦዲቱ ወቅት ከውጭ ሀገር ተገዝተው ገቢ ከተደረጉት መገልገያ ዕቃዎች ውስጥ ስምንት EPSON stylus printer ቀለም በተጠየቀው መሰረት አለመቅረቡ ታህሳስ 24 ቀን 2005 ዓ.ም ከቅድመ ህትመት ቡድን በተፃፈ ማስታወሻ ሪፖርት መደረጉን፣ M/S Lithioplate S.A ከተባለው አቅራቢ ኩባንያ ተገዝቶ ገቢ የተደረገው Negetive plate Develoer የተባለ ጥሬ ዕቃ በስፔስፊኬሽኑ መሰረት ገቢ ባለመሆኑ ከ 800-2000 ዙረት ከዞረ በኋላ ፅሁፉ የሚጠፋ (fade) የሚያደርግ በመሆኑ ተገቢውን አገልግሎት ሊሰጥ አለመቻሉን፣ የግዢ ጥያቄ ሲቀርብ የተጠየቁ ስምንት ዓይነት Epson ink cartridge የተባሉ ዕቃዎች ተገዝተው ወደ መጋዘን ሲገቡ በቁጥርና በዓይነት የተለዩ በመሆናቸው ለሥራ አመቺ ሆኖ አለመገኘቱን የአታሚና አሳታሚ ዳሬክቶሬት በዳብዳቤ ማሳወቁን ለመረዳት ተችሏል፡፡

64. ከግንጪ (አንሞል) ወረቀት ማምረቻ የሚገዙት ወረቀቶች በተደጋጋሚ የጥራት ችግር የሚያጋጥማቸው መሆኑን፣ ሁለት ወረቀቶች የሚገናኙበት መገጣጠሚያ ላይ በተገቢው መልኩ ባለመለጠፋ ወረቀቶቹ በህትመት ሥራ ላይ እያሉ እንደሚበጠሱ በደብዳቤ ቁጥር 27/94/22/30 እና 24/22/22/30 ከአታሚና አሳታሚ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለዋና ዳይሬክተሩ እና ለግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከተፃፈ ደብዳቤ እና ከአታሚና አሳታሚ

ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተወካይ እና ከግዥ ቡድን መሪ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

65. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ዕቃዎቹ ሲገዙ በተጠየቀው መሰረት መግዛትና ወደ መጋዘን ሲገቡም በተጠየቀው መሰረት መሆኑ ተረጋግጦ ሊሆን እንደሚገባ፣ ነገር ግን አልፎ አልፎ የተጠቀሱት አይነት ችግሮች እየተከሰቱ ቢሆንም በየወቅቱ የእርምት እርምጃ እየተወሰደና በተቻለ መጠን ችግሩን ለመቀነስ የግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደቶችን እንደገና ለማደራጀትና ቁጥጥሩንም የበለጠ ለማጠናከር እየተሞከረ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

66. አንሞል የወረቀት ማምረቻን በተመለከተ የሚያመርተው ወረቀት የጥራት ችግር የሚታይበት ቢሆንም ከሌላ ለመግዛት አማራጭ ባለመኖሩ የወረቀት አምራቹ ችግሩን እንዲያሻሽል ግብረ መልስ በመስጠትና በመመካከር ችግሩን እንዲቀርፍ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

67. ጥሬ ዕቃዎች ተገዝተው ገቢ ሲደረጉ በስፔስፊኬሽናቸው መሰረት መሆኑ ባለመረጋገጡ በሚመረተው ምርት ላይ የጥራት ችግር እና በሥራው ላይ መጓተት ከማስከተሉ በተጨማሪ የሀብት ብክነትን ያስከትላል፡፡

ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው ገቢ መደረጋቸውን በተመለከተ፤

68. ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር ተገዝተው የሚመጡ ንብረቶችን የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተዘጋጅቶላቸው እቃ ግምጃ ቤት ገቢ ተደርገው አስፈላጊው ምዝገባ ሊከናወንላቸው ይገባል፡፡

69. በኦዲቱ ወቅት በታህሳስ 2005 ዓ.ም ከውጪ ተገዝተው መጋዘን የገቡ ዕቃዎች (Epson ink cartridge) ከሁለት ወራት በኋላ በየካቲት ወር 2005 ገቢ እንዲሆኑ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. ለአምቦ ዩኒቨርስቲ ተሰራጭቶ የነበረ 600 ቁልፍ ጥራት የሌለው በመሆኑ ተመላሽ ሲደረግ የገቢ ደረሰኝ ሳይዘጋጅለት በዕቃ ግምጃ ቤት መቀመጡ፣ ድርጅቱ በ2004 የትምህርት ዘመን ለተከፈቱት አስር ዩኒቨርስቲዎች የተለያዩ ፈርኒቸሮችን ሰርቶና ገዝቶ ለማቅረብ በተፈፀመው ውለታ መሰረት ለተሰሩት የ15,547 ቁምሳጥኖች በ2004 በጀት አመት መግቢያ ላይ ከተገዙት 31,294 ቁልፎች ውስጥ 8,575 በወቅቱ ገቢ የተደረጉ ሲሆን፣ 18,719 ቁልፎች የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ከአንድ አመት ከስድስት ወር በላይ

በመጋዘን ከተቀመጡ በኋላ በግንቦት 2005 ገቢ የተደረጉ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ 4,000 ቁልፎች ግን ገቢ የተደረጉበት ማስረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

71. የአስሩ ዩኒቨርስቲዎችን የፈርኒቸር ምርት ሥራ እንዲሰሩ ከተሰጣቸው የውጭ የፈርኒቸር አምራቾች ውስጥ Cai Runling C/M/F/factory የተባለው ድርጅት አብዛኛዎቹን ፈርኒቸሮች በተለያየ ምክንያት በውለታው መሰረት ለዩኒቨርስቲዎቹ ባለማስረከቡ ተመላሽ ያደረጋቸው ዘጠኝ አይነት የፈርኒቸር ጥሬ ዕቃዎች በገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይሆኑ መቆየታቸውን እና ጥሬ ዕቃዎቹ በማስታወሻ እየተያዙ በሥራ ላይ እየዋሉ መሆኑን ከደብዳቤ ቁጥር 50/1095/1/27 እና ለመጋዘኑ ኃላፊ ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

72. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ንብረቶች ገቢ ሳይሆኑ የሚዘገዩበት ምክንያት የተገዛው ዕቃ እስኪረጋገጥ፣ አንዳንድ ጊዜም ከሌላ ቦታ በሚመጣ ባለሙያ ኢንስፔክሽን ካልተሰራ አንረከብም በሚል ሲሆን፣ ይህ መፈራራት የሚፈጥረው ችግር መሆኑን፣ ነገር ግን መታረም የሚገባው በመሆኑ ድርጅቱ ለማሻሻል ጥረት እንደሚያደርግ፣ በቁልፎቹ ላይ የተፈጠረውን ችግር ርካሽ ዋጋ ያለው ቁልፍ በመመረጡ መሆኑን፣ ከተከሰተው ችግር ለመማር እንደተሞከረና ዕቃው ገቢ ሆኖ በቀጣይ አግባብ ላለው ሥራ ጥቅም ላይ እንዲውል እየተሰራ መሆኑን፣ የአስሩ ዩኒቨርስቲዎችን የፈርኒቸር ምርት ሥራ እንዲሰራ የተሰጠውን Cai Runling C/M/F/factory የተባለው ድርጅት ሥራውን ለመስራት የተዋዋለና ጥሬ ዕቃ የተሰጠው ቢሆንም ሥራውን በሚፈለገው ጥራትና መጠን ባለመሰራቱ የወሰደውን በርካታ ጥሬ ዕቃ እንዲመልስ የተደረገ መሆኑን እና እስኪጣራ ድረስ ለሰራው ሥራ ክፍያ ያልተፈጸመ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

73. ድርጅቱ የተገዙትን እና ተመላሽ ተደረጉትን ዕቃዎች በተገቢው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ እንዲሆኑ አለማድረጉ ንብረቶቹን ለመቆጣጠር ካለማስቻሉም በላይ ለብክነትና ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

የትምህርት መሳሪያዎችን ለማምረት፣ ለማሻሻልና ጥራታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል ጥናትና ምርምር መካሄዱን በተመለከተ፤

74. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎችን ለማምረት፣ ለማሻሻልና ጥራታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል ጥናትና ምርምር ማካሄድ እንዲሁም አዳዲስ ዲዛይኖችንና አሠራሮችን በመዘርጋት ሥራ ላይ ማዋል አለበት፡፡

75. ድርጅቱ የምርት ውጤት የሚሻሻልበትንና የሚያድግበትን ሁኔታ እንዲሁም የአሰራር ዘዴው በየጊዜው ካለው የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር አብሮ የሚራመድበትን መንገድ በማጥናት፣ ለድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ ዕድገት ጠቃሚ ናቸው የሚባሉትን የማሻሻያ የጥናት ውጤቶች በመለየት ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ዙሪያ ክፍተት እንዳለበት በኦዲቱ ወቅት ከተከለሰ የሥራ አመራር ቦርድ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 05/2004 ለመረዳት ተችሏል፡፡

76. ከዚህም በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የክልል የትምህርት ቢሮዎች፣ የትምህርት ጽ/ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች እና ትምህርት ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅቱ መፃህፍትን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ባነሮችን፣ ለህፃናት የሚሆኑ ማስተማሪያዎችን እና ከ9ኛ ክፍል በላይ ለሆኑ ተማሪዎች የሚሆን የላቦራቶሪ ዕቃዎችን ማቅረብ ቢኖርበትም ሊያቀርብ አለመቻሉን እና ከ20 ዓመት በፊት የነበረ የሳይንስ ኪትስ እስካሁን ድረስ ያልተሻሻለ መሆኑን፣ ድርጅቱ ባለ ቀለም መፅሀፍት ህትመት የሚወዳደር ቢሆንም አሸንፎ አለማወቁን ለዚህም ምክንያቱ ሰፋ ያለ ጥናት ባለማከናወኑ መሆኑን እና ድርጅቱ ምንም አይነት ጥናት ለማጥናት ጥረት አድርጎ እንደማያውቅና አዳዲስ ዲዛይኖች ቀርበውላቸው እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡

77. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ችግሩ መኖሩን በመገንዘብ በአሁኑ ወቅት የጥራት የምርምርና ሥርዓት አገልግሎት እንዲቋቋም በማድረግ የሰው ኃይል በማሟላትና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ላይ እንደሚገኙና በቀጣይ በዚህ ረገድ ድርጅቱን ለማጠናከር እንደሚሞከሩ፣ በአሁኑ ወቅት የመማሪያ መፅሀፍት በአብዛኛው በትምህርት ቢሮዎች አሳታሚነትና በት/ቤቶች አማካኝነት ስለሚሰራጩ በድርጅቱ በኩል ሽያጭ እየቆመ እንደሆነና በሽያጭ ጣቢያዎች ቀደም ሲል የነበሩና የመማሪያ ጊዜ ያለፈባቸው መፃህፍት መኖራቸው እንደማይቀርና ከሥር ከሥር እየተጣራ እንዲወገዱ የሚደረግ መሆኑን፣ ሌላው ባለቀለም መፅሀፍ ለማተም የሚችል ማሽን የሌለ በመሆኑ ሥራ የሚያዘው በውድድር ስለሆነና ድርጅቱ ሊያሸንፍም ላያሸንፍም የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልና ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት ከኦሮሚያ ት/ቢሮ የ99 ሚሊየን ብር ህትመት ድርጅቱ አሸንፎ እየሰራ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

78. የምርት ውጤቶችን ሊያሳድጉ የሚችሉ ጥናትና ምርምሮችን አለማድረግ፣ አዳዲስ ዲዛይኖችና አሰራሮች እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የመጠቀም ሁኔታ አለመኖሩ

የደንበኞችን ፍላጎት ለማሟላት ካለማስቻሉም በላይ ድርጅቱ በሚያመርታቸው ምርቶች ላይ ያለውን ችግር በመለየት ምርቶችን እንዳያሻሽል እና በገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

ድርጅቱ ልዩ ልዩ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቱን በተመለከተ፤

79. ድርጅቱ የመማርያና የማስተማሪያ መፃሐፍትን ልዩ ልዩ ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ ጽሑፎችን፣ ቻርቶችን፣ ካርታዎችንና ሥዕላዊ መግለጫዎችን እንዲሁም ለመዋለ ሕፃናት፣ ለሙዚቃ፣ ለሥነ ጥበብ እና ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አሰጣጥ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ሊያመርት ይገባል፡፡
80. ይሁን እንጂ ድርጅቱ ለትምህርቱ ዘርፍ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችሉ ምርቶችን ለምሳሌ ለሙዚቃ፣ ለሥነ ጥበብ እና ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አሰጣጥ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች፣ ካርታዎች፣ ስዕላዊ መግለጫዎች የማያመርት መሆኑን፣ ለሽያጭ የሚሆኑ የሪፈረንስ መፃህፍት በበቂ ሁኔታ ለቅርንጫፉ የሚላኩበት ሁኔታ አለመኖሩ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
81. ከዚህም በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ የትምህርት ጽ/ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች እና የትምህርት ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅቱ ቀደም ሲል መማሪያና ማስተማርያ መፃህፍትን፣ ፈርኒቸሮችን፣ ማንዋል፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ የሳይንስ ኪት መጫወቻዎችና የመሳሰሉትን ያመርት እንደነበር በአሁኑ ሰዓት ግን ለትምህርት ቢሮዎች የሚያመርተው ምርት አልፎ አልፎ የህትመት ውጤቶችን ብቻ መሆኑንና ከላይ በተጠቀሱት ምርቶች ላይ ድርጅቱ እንዲሳተፍ ቢፈልጉም በሚያወጡት ጨረታ ላይ እንደማይሳተፍ፣ የላቦራቶሪ ዕቃዎች አቅርቦት በተለይ ለሁለተኛ ደረጃ የሚሆን በጣም ዝቅተኛ መሆኑን፣ በሽያጭ ጣቢያው የሚገኙ መፃህፍቶችም ጊዜ ያለፈባቸው በመሆናቸው ለአሁኑ የትምህርት ሥርዓት የማይጠቅሙ መሆናቸውን፣ ትምህርት ቢሮዎች ለመፃህፍት ጨረታ ሲያወጡ ድርጅቱ እንደማይሳተፍና በርካታ መፃህፍቶችን እንዲያትም ቢጠይቅም ከማሽን አለመኖርና ከአቅም ማነስ የተነሳ ሁሉንም ህትመት እንደማያከናውን ገልጸዋል፡፡
82. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ድርጅቱ ሥራዎችን የሚሰራው የተሻለ ሽያጭና ትርፍ ይኖራል ብሎ ሲያምንና

ለድርጅቱ የሚያዋጣ ዋጋ ሰጥቶ በጨረታ በመሳተፍ ሲያሸንፍ መሆኑን፣ በዚህ መልኩ በአሁኑ ሰዓት ድርጅቱ የመረጣቸውን የተለያዩ የህትመትና የፈርኒቸር ሥራዎች እየሰራና የታቀደውን የምርት፣ የሽያጭና የትርፍ መጠን እያሟላ መሆኑንና በቀጣይነት የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚጥር፣ ሆኖም የድርጅቱ የማምረት አቅም ሁሉንም ት/ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎችና ት/ቢሮዎች ማዳረስ የማይችል በመሆኑ፣ ጨረታ የሚሳተፈውም ሆነ የሚሰራው በአቅሙ መጠን በመሆኑ ምክንያት አንዳንድ ባለድርሻ አካላት ድርጅቱ ተደራሽ አይደለም ቢሉ እውነትነት ያለው እንደሆነና ድርጅቱ አቅሙን በማሻሻል ተደራሽ ለመሆን እንደሚጥር ገልፀዋል፡፡

83. ድርጅቱ ለትምህርቱ ዘርፍ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶች በበቂ ሁኔታ በማምረት ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ያለመቻሉ፣ የደንበኞች ፍላጎት ያለማሟላቱ ደንበኛን የሚያርቅበት ከመሆኑም በላይ በገበያ ላይ በበቂ ሁኔታ ተወዳዳሪ ሆኖ "ለመማሪያና ማስተማሪያ አጋዥ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና የህትመት ውጤቶችን በማምረት ቀዳሚ ተቋም ሆኖ መገኘት" የሚለውን ራዕይ እንዳይሳካ ያደርገዋል፡፡

ድርጅቱ የሠራተኞችን ክህሎት በመደበኛ ትምህርትና በስልጠና ማሣደጉን በተመለከተ፤

84. ድርጅቱ የሰው ኃይሉን በተለይ በግዥ፣ በምርት ሂደትና በስርጭት ላይ ያሉትን ሠራተኞች ክህሎት በመደበኛ ትምህርትና በስልጠና ማሣደግ ይኖርበታል፡፡

85. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና መጠይቅ ከቀረበላቸው የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች ለመረዳት እንደተቻለው የግዥ ሂደቱን ለማሻሻል ለግዢ ክፍሉ ስልጠና የተሰጠበት ሁኔታ እንደሌለ፣ በየሥራ ዘርፉ የሚያስፈልገው የስልጠና አይነት ቢለይም በታቀደለት መሰረት የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና እንዲሰጥ አለመደረጉን፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሀገር ውስጥ የህትመት ባለሙያዎችን የሚያሰለጥን ተቋም ባለመኖሩ የህትመቱ ሥራ የሚከናወነው በልምድ ብቻ መሆኑን፣ በህትመት ሥራ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰራተኞች እና የጥገና ባለሙያዎች ለህትመት ከተገዙ አዳዲስ ማሽኖች ጋር ለመተዋወቅ ተገቢው ስልጠና ያልተሰጣቸው በመሆኑ ማሽኑ ተበላሽቶ መጠገን ባለመቻሉ ለረጅም ጊዜ ሳይሰራ የቆየበት ሁኔታ መኖሩ፣ በቡድን በማደራጀት የውስጥ ለውስጥ ስልጠና የሚሰጥ ቢሆንም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ስልጠናው በቂ አለመሆኑን እና የሳይንስ ኪት ምርት ሂደት ላይ ጠርሙስ (ግላስ) ለመስራት የሚችሉ ሰራተኞች ባለመኖራቸው ውስጥ ለውስጥ የማሰልጠን ስራ ለመስራት እየተሞከረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

86. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ድርጅቱ በዕቅድ የያዘውን ሥልጠና ለመስጠት ጥረት እየተደረገ እንደሆነና ከታቀደው ውጭ በርካታ ሥልጠናዎች መስጠታቸውን የድርጅቱ አፈፃፀም እንደሚያሳይ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ይህንን በተመለከተ ማስረጃ ሊቀርብልን አልቻለም፡፡

87. ድርጅቱ በተለይ በምርት በግዢ እና በሽያጭ ሥራ ላይ ያሉ ሰራተኞች ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ አለመደረጉ ሰራተኞች ሥራቸውን በብቃትና በጥራት እንዳያከናውኑ ከማድረጉም በላይ ድርጅቱ አዳዲስና ዘመናዊ አሰራሮችን በማምጣት የተቋቋመበትን ዓላማ እንዳያሳካ ያደርገዋል፡፡

ድርጅቱ ምርቶችን በተገባው ውለታ መሰረት ለደንበኞች ማስረከቡን በተመለከተ፤

88. ድርጅቱ ያመረታቸውን ምርቶች በገባው ውለታ መሰረት በጥራትና በጊዜ ገደብ ለደንበኞች ማስረከብ አለበት፡፡

89. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው የሥራ ኃላፊዎች ከሰጡት መልስ በፈርኒቸር ምርት ላይ የጥራት ችግር በጣም እየሰፋ መሄዱን፣ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የመፃህፍት ህትመት ሥራ ውለታ ከተገባው የጊዜ ገደብ 103 ቀናት የዘገየ መሆኑን፣ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር የተደረገው የመፃህፍት ህትመት በውሉ ላይ ከተገለጸው የማስረከቢያ ጊዜ ገደብ በላይ 106 ቀናት መዘግየቱን፣ የአፋር ትምህርት ቢሮ ያዘዛቸው መፃህፍት በውለታው መሰረት ባለመጠናቀቃቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያመጣው ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን፣ ድርጅቱ ከትምህርት ቢሮዎች ጋር በገባው ውለታ መሰረት የመማሪያ መፃህፍት አትሞ ለማስረከብ አለመቻሉን፣ ባለፉት ሁለት አመታት የህትመት ግብዓት ወረቀት፣ ኮላ፣ ፕሌት መሳሰሉት በክምችት ባለመያዙ ከአንሞል ፕሮዳክት ኢትዮጵያ ብቻ በሚገኝ ወረቀትና በቁጥ ቁጥ ግዥ በሚቀርበው ኮላ በሙሉ አቅም ማተም አለመቻሉን፣ በ2005 ዓ.ም በጨረታ የተገኘ የትግራይ ትምህርት ቢሮ የመፃህፍት ህትመት የጥራት ጉድለት በመታየቱ በድርጅቱ ላይ 1.8 ሚሊየን ብር ኪሳራ ማስከተሉን፣ የኢትዮጵያ እስላማዊ ልማት ማህበር ልዩ ልዩ ፈርኒቸሮችን ለመግዛት በቅድሚያ ብር 130,826.77 ከፍሎ አብዛኛው ፈርኒቸር የተረከበ ቢሆንም የተወሰነውን ከማስረከቢያው ቀን በኋላ 68 ቀናት ዘግይቶ መረከቡን ለመረዳት ተችሏል፡፡

90. ይህንንም በተመለከተ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት አስተያየት የታዘዙ ምርቶችን በውሉ መሰረት በወቅቱ የማድረስ ችግር በተደጋጋሚ

እንደታየና ይህም አግባብ ባለመሆኑ ሥራዎችን በአቅም መጥኖ በመያዝ የጥሬ ዕቃ አቅርቦትና የአሰራር ባህልን በማሻሻል የደንበኛ ትዕዛዝን በወቅቱ ለማድረስ ጥረት እየተደረገ መሆኑንና የተወሰነ መሻሻል እንደታየ በቀጣይም የበለጠ ጥረት እንደሚደረግ ገልፀው፣ ድርጅቱ የአቅም ውስንነት ያለበት በመሆኑ አንዳንድ ሥራዎችን ሳለመቀበል የሚገደድ ከመሆኑም በላይ በምርት ሂደት ላይ የጥራት ጉድለቶችን በወቅቱ ባለማጤን የተከሰቱ ችግሮች መኖራቸውን እና ከዚህም ችግር ለመማር የተቻለ መሆኑን፣ የማስተካካያ እርምጃ እንደተወሰደና የተበላሹ ምርቶች ለደንበኛው እንዳይተላለፍ የተደረገበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡

91. ድርጅቱ ምርቶችን ከደንበኞች ጋር በተዋዋለበት ወቅት እና በጥራት ካላቀረበ ደንበኞች በድርጅቱ ላይ እምነት በማጣት ወደ ሌሎች አቅራቢዎች እንዲሄዱ ከማድረጉም በላይ በመማር ማስተማሩ ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

ድርጅቱ ምርቶች በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሰረት ለደንበኞች ማስረከቡን በተመለከተ፣

92. ድርጅቱ የሚያመርታቸው ምርቶች በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሰረት ተመርተው ለደንበኞች መሠጠት አለባቸው፡፡

93. በ2003 ዓ.ም ለፈርኒቸር መስሪያ የተገዛው ፎርማይካ በተጠየቀው መሰረት ባለመቅረቡ በጥያቄው መሰረት ለቀረበው ፎርማይካ ደንበኛው ሂሳቡን የከፈለ ሲሆን በስፔስፊኬሽኑ መሰረት ያልቀረበው እንዲመለስ የጠየቀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. ከዚህም በተጨማሪ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በ2004 ዓ.ም ከድርጅቱ የተረከቡአቸው ሎከሮች /ቁምሳጥኖች/ ጥራት የሌላቸውና በቀላሉ የሚገነጣጠሉ እንዲሁም የአንዱ ቁልፍ የሌላውን የሚከፍት መሆኑን ሲገልፁ፣ የደጃች ወንድራድ የመ/ደ/ትምህርት ቤት የሥራ ኃላፊዎች የሪፖርት ካርድ (የተማሪዎች ሰርተፊኬት) በስፔስፊኬሽን መሰረት አለመሰራቱን ይህም የትምህርት ቤቱን ስም በሌላ ትምህርት ቤት ስም ተቀይሮ የታተመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

95. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ምርትን በሚፈለገው የጥራት ደረጃ የማምረትና የመቆጣጠር አቅምም ሆነ የሥራ ባህል ችግር እንዳለና ይህን ችግር ለመፍታት ተከታታይ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

96. ምርቶች በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሰረት አለመመረቱ በድርጅቱ ላይ የንብረት ብክነት እና ተጨማሪ ወጪ ከማስከተሉም በላይ የደንበኞችን እርካታ ይቀንሳል፡፡

የድርጅቱ ማሽኖች የሥራ ፍሰታቸውን በመጠበቅ በአንድ ቦታ መተከላቸውን በተመለከተ፤

97. የድርጅቱ ማሽኖች የሥራ ፍሰታቸውን በመጠበቅ በአንድ ቦታ መተከል አለባቸው፡፡

98. የድርጅቱ ማተሚያ ቤትና ዋናው መ/ቤት በተራራቀ ቦታ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ከፍተኛ የሥራ አመራር ችግር፣ የወጪ ጫና እና በሰው ኃይል አጠቃቀም ላይ ችግር ያስከተለ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህትመቱ ፅሁፍ ከሚቀረፅበት ከኮምፒውተር ክፍል አንስቶ እስከ ፕሌት ዝግጅት ድረስ በሽሮ ሜዳው ማተሚያ ቤት ተዘጋጅቶ ወደ ዋናው መ/ቤት ማተሚያ ቤት ሄዶ እንደሚታተም እንዲሁም በዋናው ማተሚያ ቤት አራት አይነት ቀለም የያዘ ህትመት ታትሞ ወደ ሽሮ ሜዳ ማተሚያ ቤት በመሄድ መጽሀፉ እንደሚዘጋጅ በአካል ተገኝቶ በማየትና ከሥራ ኃላፊዎች ከተደረገ ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

99. ስለሁኔታው የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የችግሩ ጥልቀት ከተጠቀሰውም በላይ እንደሆነና ይህንን የቆየ ችግር ለመፍታት መስሪያ ቤቱን በአንድ ቦታ ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

100. ድርጅቱ ተከታታይ የሥራ ፍሰት ያላቸውን የህትመት ማሽኖች በሁለት ቦታ ማለትም በሽሮ ሜዳና በዋናው ግቢ መትከሉ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን ከማናሩም በላይ በምልልስ የሚባክነው ጊዜ በምርት ሥራ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

ድርጅቱ ከትምህርት ዘርፎች ጋር ግንኙነት መፍጠሩን እና ለደንበኞች በሚሰጠው አገልግሎት ግብረ መልስ መሰብሰቡን በተመለከተ፤

101. ድርጅቱ ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከሚመለከታቸው የትምህርት ዘርፎች፣ የግልና የመንግስት ድርጅቶች፣ ተቋማትና መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የቴክኒክ ድጋፎችን በመለዋወጥ በጋራ መስራት እና ለሽያጭ ምርት እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ፣ በሚሰጠው የግዢ አገልግሎት የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ ለመሆኑ ግብረ መልስ መቀበል ይኖርበታል፡፡

102. በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የቴክኒክ ድጋፎችን በመለዋወጥ በጋራ የሚሰራበት እና ለሽያጭ

ምርት እድገት አስተዋፅኦ የሚያደርግበት ሁኔታ በቂ እንዳልሆነ እና የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ ለመሆኑ ግብረ መልስ አለመሰብሰቡን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

103. ይህንንም በተመለከተ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከድርጅቱ ጋር ምንም የስራ ግንኙነት የሌላቸውና ከ1992 እስከ 1998 ዓ.ም አንዳንድ ቁሳቁሶች ለምሳሌ ኬሚካል፣ ቾክ እና የመሳሰሉትን የሚገዙበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት ግን የነበረው የስራ ግንኙነታቸው የተቋረጠበት ሁኔታ መኖሩን ሲገልጹ፣ የትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች ከድርጅቱ ጋር ምንም አይነት በቅንጅት የሚሰራ ሥራ እንደሌለና ጨረታ ሲወጣም ድርጅቱ ተሳትፎ እንደማያደርግ ገልጸዋል፡፡

104. ከዚህም በተጨማሪ ከድርጅቱ ሽያጭ ጣቢያ የአዋጭነት ጥናት ላይ በድርጅቱ ካሉት የሽያጭ ጣቢያዎች የተሻለ የሥራ አፈፃፀም ካላቸው ሌሎች አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር አለመቻሉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

105. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ቅንጅትና ትስስር መፍጠር አግባብ በመሆኑ በመርህ ደረጃ የሚቀበሉት እንደሆነና ድርጅቱ ትብብርና ቅንጅታዊ አሰራር መመስረት ከሚገባው ለምሳሌ መቱ ዩኒቨርስቲ፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ፣ ኦሮሚያ ት/ቢሮ፣ ሐረሪ ት/ቢሮ፣ ሱማሌ ት/ቢሮ ወዘተ ጋር ተቀናጅቶ እንደሚሰራ፣ በአሁኑ ወቅት ከመንግስት ማተሚያ ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ፣ መሳሪያ በመዋዋስ፣ የጋራ ግዥ አብሮ በመፈፀም በቅንጅትና ትስስር እየተሰራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

106. የግዥ አገልግሎትን በተመለከተ የድርጅቱ ዋና ሥራ ካለመሆኑም በላይ አዋጭነት የሌለው፣ የድርጅቱን የገንዘብ አቅም የሚፈታተንና የደንበኛው እርካታ ያልተገኘበት ሥራ ሆኖ በመቆየቱና ይህንን በመገንዘብ ከዚህ ሥራ በመውጣት ድርጅቱ በዋናው ሥራ ላይ ማተኮር እንዳለበት ታምኖበት ከዚህ ሥራ ለመውጣት ስለተወሰነ የተጀመሩ ሥራዎችን ከማጠናቀቅ ውጭ አዲስ ሥራ እንደማይያዝ በ2006 በጀት አመት ዕቅድ ላይም እንዳልተካተተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ አስረድተዋል፡፡

107. ድርጅቱ በሚያመርታቸው ምርቶችና በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዙሪያ ከሚመለከታቸው የግልና የመንግስት ድርጅቶች፣ ተቋማትና መ/ቤቶች ጋር የስራ ቅንጅትና የቴክኒክ ድጋፎች ማድረግ ያለመቻሉ እና ከደንበኞች ግብረ-መልስ ያለመሰብሰቡ የተሻለ የሥራ ልምድን ለመቅሰምም ሆነ ለመለዋወጥ እንዳይችል ከማድረጉም በላይ የድርጅቱ ዕውቅና እና የአገልግሎት ጥራት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ፤

108. ድርጅቱ ተሰብሳቢ ሂሳቡን በወቅቱና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልክ መሰብሰብ አለበት፡፡

109. በኦዲቱ ወቅት በ2002 በጀት አመት በውጭ ኦዲተሮች ከቀረበ ሪፖርት በመነሳት ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ በ2004 በጀት ዓመት ለማጣራት መርሀ ግብር ተዘጋጅቶ የፀደቀ ቢሆንም የተደረገ እንቅስቃሴ እንደሌለ ይህም በመሆኑ ከ2003 እስከ 2005 ዓ.ም እየተንከባለለ የመጣ ብር 54,883,189.60 ተሰብሳቢ ሂሳብ እንደሚታይ ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 4 ተያይዟል)

110. በ2004 በጀት ዓመት ከውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 10,500,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ ለመሰብሰብ የተቻለው ብር 1,510,079.35 (14%) ብቻ ሲሆን፣ በ2005 በጀት ዓመት ከውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 10,500,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ ለመሰብሰብ የተቻለው ብር 1,817,000 (17%) ብቻ መሆኑን ከሁለቱ በጀት ዓመታት ዕቅድ አፈፃፀም ለመረዳት ተችሏል፡፡

111. በድርጅቱ የሽያጭ መመሪያ የዱቤ ሽያጭ የሚጠይቅ ማንኛውም ሚኒስቴር መ/ቤት ወይም በመንግስት በጀት የሚተዳደር ድርጅት አግባብ ባለው ኃላፊ የተፈረመና የድርጅቱ ማህተም ያለበት የሥራ ትእዛዝ አቅርቦ በቅድሚያ ዕዳ የሌለበት መሆኑ በፋይናንስ መምሪያ በጥንቃቄ ተረጋግጦ ዱቤው እንዲሰራ የሚያዝ ቢሆንም ዕዳ እንዳለባቸው እየታወቀ ለኦሮሚያ፣ ለሀረሪ፣ ለትግራይ እና ለአማራ ትምህርት ቢሮዎች፣ ዱቤ የተሰጠ መሆኑን ከተከለሱት ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

112. ከዚህም በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- ✓ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ከ1991 እስከ 2001 ዓ.ም ከድርጅቱ ለተረከባቸው የተለያዩ ሥራዎች ብር 10,040,126.20 ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ያልከፈለ ሲሆን፣ በአጠቃላይ በህዳር 30 2006 ዓ.ም ተሰብሳቢ ሂሳብ ሌጀር ላይ የሚታይ ብር 41,544,526.20 ከትምህርት ቢሮው ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- ✓ ትምህርት ሚኒስቴር ለልዩ ልዩ የ10ኛ ክፍል መፃህፍትና ለታሪክ ሞዱዩልስ ለትግሪኛ ቋንቋ ብር 196,524.74 የህትመት ዋጋ ሳይከፈል በመቅረቱ በድርጅቱ ክስ የተመሰረተ ሲሆን፣ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም የተሰብሳቢ ሌጀር ላይ ከትምህርት ሚኒስቴር ያልተሰበሰበ ብር 4,275,701.36 መኖሩ፣
- ✓ ድርጅቱ የአሰራር ሥርዓት የመፃህፍት ሽያጭ ወኪሎች ዋስትና ስለማያቀርቡ ከብር 10,000 ያልበለጠ ዋጋ ያላቸው መፃህፍት እየተሰጣቸው ሸጠው ገቢ ማድረጋቸው እየታየ እንዲሰጥ የሚፈቅድ ሲሆን፣ ለአሽናፊ መፃህፍት መሸጫና

ማከፋፈያ ድርጅት በ1999 እና በ2000 ዓ.ም ዋስትና ሳይኖረው ብር 354,765.50 ዋጋ ያላቸው መፃህፍት ተሰጥቶት ከዚህ ውስጥ ብር 78,122.85 በጥሬ ገንዘብና በአይነት ገቢ ሲያደርግ ብር 276,642.05 ገቢ ባለማድረጉ በድርጅቱ ክስ መመስረቱን እና ለዳኝነትና ለቴምብር ቀረጥ ድርጅቱ ያወጣውን ብር 5706.42 በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ለማስጠት የመፃህፍት መደብሩ ባለቤት ሳይገኝ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ስለማይሰጥ የመደብሩን ባለቤት መገኘትና ፍርድ ቤት መቅረብ እየጠበቀ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

113. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ላይ በሰጡት አስተያየት በድርጅቱ ደካማ የደንበኞች አገልግሎትና የፋይናንስ ሥርዓት እንዳለ መታየቱን፣ ይህንንም ለማሻሻል የድርጅቱን አደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት በመፈተሽ የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከግዥ ሥራ ተነጥሎ ለብቻው ተጠናክሮ እንዲደራጅ መደረጉን፣ እንዲሁም ውዝፍ ሥራዎችን አጥርቶ ወቅታዊ ሥራዎችን ለመፈፀም ጥረት እየተደረገ እንደሆነ፣ በድርጅቱ በርካታ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ለረጅም ጊዜ የቆዩበት ምክንያት በክትትል ማነስ፣ በደንበኛው በኩል ለመክፈል አለመፈለግና አለመቻል ወዘተ ሲሆን፣ ወቅታዊ ሂሳቦች እንዳይወዘፉ ጥረት እየተደረገና የቆዩ ሂሳቦችንም በድርድርም ሆነ በህግ እልባት ለመስጠት እየተሞከረ እንደሆነ፣ ነገር ግን ዕዳ ካለበት ድርጅት ጋር አንሰራም ማለቱ ድርጅቱን የሚጎዳ በመሆኑ ዕዳውን ለመሰብሰብ በመሞከር ላይ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

114. በተጨማሪም የውክልና ሽያጭን በተመለከተ በአሁኑ ወቅት እየቆመ ያለ ሥራ እንደሆነ፣ ነገር ግን ቀደም ሲል የተሰጠው የውክልና ውልም ሆነ የሰነድ አያያዝ እንዲሁም የክትትል ሥርዓት ችግር ያለው በመሆኑ በእንጥልጥል ያሉ ጉዳዮችን በህግም ሆነ በድርድር እልባት ለመስጠት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ፣ ሆኖም ሊሰበሰቡ የማይችሉትን ባለው መመሪያ መሰረት መጠባበቂያ ለመያዝና ለመሰረዝ በሚያስችል መልኩ እርምጃዎች እየተወሰዱ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

115. ድርጅቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በወቅቱ ያለመሰብሰቡ ለድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ ሊሆን የሚችል ከፍተኛ ገንዘብ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

ድርጅቱ ምርትና አገልግሎቱን የማስተዋወቅ ሥራ ማከናወኑን እና ውጤቱን መገምገሙን በተመለከተ፤

116. ድርጅቱ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ፣ በህትመት ውጤቶች፣ በሽያጭ ሠራተኞች፣ በባዛር፣ በኢግዚብሽንና በመሳሰሉት በመጠቀም ምርትና አገልግሎትን የማስተዋወቅ ሥራ

ወጥ በሆነ መልኩ ማከናወን እና የተከናወኑትን የማስተዋወቅ ሥራዎች ውጤት መገምገም አለበት፡፡

117. ድርጅቱ ምርትና አገልግሎቱ ላይ የሚያደርገው የማስተዋወቅ ሥራ በቂ አለመሆኑን፣ የሽያጭ ማስፋፊያና የገበያ ጥናት ሥራ በበቂና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ባለመካሄዱ ምክንያት በሽያጭ ጣቢያዎች ያለው ሽያጭ አጥጋቢ አለመሆኑን፣ በሽያጭ ጣቢያዎች ለሽያጭ መቀነስ በዋናነት የሚጠቀሱት ከድርጅቱ የአቅርቦት ማነስ፣ ጨረታዎችን ማሸነፍ አለመቻል እንዲሁም ሽያጭ ጣቢያዎች ባሉበት ከተሞች በራሪ ፅሁፎችን እና ሳምፕል በመጠቀም ገበያ የማስተዋወቅ በቂ ሥራ አለመካሄዱ ለፕሮሞሽን ሥራ አለመጠናከር እንደ ምክንያት እንደሚጠቀስ በድርጅቱ ከተዘጋጀው የሽያጭ ጣቢያ የአዋጭነት ጥናት ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

118. በናሙና ተመርጠው ቃለ-መጠይቅ ከቀረበላቸው አስራ ሁለት ባለድርሻ አካላት ውስጥ አምስቱ ድርጅቱ የሚሰራው የማስተዋወቅ ስራ በጣም አነስተኛ እና ተወዳዳሪ ሆኖ ሊቀርብ የሚያስችለው አለመሆኑን ሲገልጹ፣ ሰባቱ ባለድርሻ አካላት ደግሞ በድርጅቱ የተሰራ ምንም የማስተዋወቅ ስራ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

119. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ትምህርት ቢሮዎች እና ክልሎች በሚያዘጋጁት የተለያዩ ዝግጅቶች ላይ ስፖንሰር እንደሚያደርጉና በተለያዩ ኢግዚቢሽኖች እንደሚሳተፉ፣ አመታዊ ካላንደር በማዘጋጀት እንደሚያሰራጩ፣ የድርጅቱን አመታዊ መፅሄት በማዘጋጀት በየአመቱ በማሰራጨት ባለድርሻ አካላት ስለድርጅቱ እንዲያውቁት እንደሚያደርጉና በድርጅቱ አነሳሽነት የመፃህፍት ሽያጭ አውደ ርዕይ ተዘጋጅቶ የሽያጭና የማስተዋወቅ ሥራ እየሰሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በቀጣይነትም ጥቅምና ወጪን በመመዘን አዋጭ ሆኖ ሲገኝ የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚሰራ፣ የማስተዋወቅ ውጤት ግምገማን በተመለከተ መሰራት እንደሚኖርበት እና በቀጣይም በተሻለ አቅም ለመስራት እንደሚሞክሩ ገልፀዋል፡፡

120. ከላይ የተጠቀሱት የማስተዋወቅ ሥራዎች የተካሄደባቸውን መረጃዎች የታዩ ቢሆንም ከድርጅቱ የመስራት አቅም አንፃር በቂ ነው ለማለት አያስችልም፡፡

121. ድርጅቱ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች፣ በህትመት ውጤቶች፣ በሽያጭ ሰራተኞች፣ በባዛርና በኢግዚብሽን ምርትና አገልግሎቱን ወጥ በሆነ መልኩ ዕቅድ አውጥቶ ማስተዋወቅ ካልቻለ የሀገሪቱን የነፃ ገበያ ውድድር ማሸነፍና መወጣት ካለመቻሉም በላይ ተጠቃሚ አካላት በሚሰጠው ምርትና አገልግሎት እንዳይረኩ

ያደርጋል፡፡ የተሰሩትንም ማስታወቂያዎች ውጤት ግምገማ አለመሰራቱ ተጠቃሚዎች በትክክል ስለድርጅቱ ምርትና አገልግሎት መረዳታቸውን ለማወቅ ካለማስቻሉም በላይ ከተገኘው ውጤት በመነሳት ሊደረጉ የሚገባቸውን ማስተካከያዎች ለመረዳት ያዳግታል፡፡

ድርጅቱ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤

122. ድርጅቱ የተሟላና ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣ በድርጅቱ ውስጥ ካሉ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች እና ከውጪ ደንበኞች ጋር የቅርብ ግኑኝነት በመፍጠር ደንበኞች ስለምርቱ ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ የዋጋ ዝርዝር፣ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡

123. ይሁን እንጂ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱን ጠንካራ ለማድረግ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ የሆነው የመረጃ መረብ በድርጅቱ አለመዘርጋቱን፣ እና በድርጅቱ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች እርስ በርሳቸው የሚገናኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን ከቀረቡልን ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

124. በተጨማሪም በናሙና የታዩ ትምህርት ቢሮዎች፣ ትምህርት መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርስቲዎች የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ መረጃን በኢንተርኔትም ሆነ በተለያዩ የመረጃ መስጫ መንገዶች በመስጠቱ ዙሪያ ከፍተኛ ችግር እንዳለ እና ድርጅቱ ስለሚሰጠው ምርትና አገልግሎት ወቅታዊ መረጃ የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

125. ይህንንም በተመለከተ የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የመረጃ ስርዓቱን በተመለከተ የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም አመርቂ ሆኖ እንዳልተገኘና በቀጣይ አቅም በፈቀደ ሁሉ ለማሻሻልና አቅም ለመፍጠር ጥረት እንደሚያደርጉ አስረድተዋል፡፡

126. በድርጅቱ ጠንካራ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ የሥራ ክፍሎቹ እርስ በርሳቸው መረጃን በወቅቱ በመቀባበል ተናበው እንዳይሰሩ፣ የድርጅቱ ባለድርሻ አካላት ድርጅቱ ስለሚመረተው ምርትና ስለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢው ግንዛቤ እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ የድርጅቱን ተፈላጊነት እና የገበያ ተወዳዳሪነት ይቀንሰዋል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

127. የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ራዕይ ለአገራችን የትምህርት ሴክተር ለመማሪያና ማስተማሪያ አጋዥ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና የህትመት ውጤቶችን በማምረት ቀዳሚ ተቋም ሆኖ መገኘት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህንን ራዕዩን ለማሳካትም የድርጅቱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት አፈፃፀምን በተመለከተ የሚከተሉት ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ✓ በግዢ ክፍሉ በሥራ ላይ ካሉት 11 ሰራተኞች 6ቱ በሥራ መደቦች የተፈላጊ ችሎታ መመዘኛ መስፈርት መሰረት የሚፈለገውን ተፈላጊ ችሎታ ያላሟሉና ቦታው የሚጠይቀው የኮምፒውተር ዕውቀት የሌላቸው መሆኑን፣
- ✓ የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት ግዥዎች በዕቅዱ መሰረት አለመፈጸማቸው፣
- ✓ የግዢ ክፍሉ የዕቅድና ክንውን መረጃዎች በተደራጀ መልኩ ያለመያዛቸው እና የግዢ ሥርዓቱን በመገምገም ፈጣን እንዲሆን ማድረግ አለመቻሉ፣
- ✓ የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ በጥሬ ዕቃና በመሳሪያዎች አለመሟላት ምክንያት የሚቋረጥ መሆኑ፣
- ✓ በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ማሽኖች ረጅም ጊዜ ያገለገሉ በመሆናቸው በተደጋጋሚ ብልሽት የሚገጥማቸውና የመለዋወጫ እጥረት መኖሩ፣ እንዲሁም የምርት ብዛትና ጥራትን የመቀነስ፣ የጥገና ወጪን የመጨመር ችግር የሚታይ መሆኑ፣
- ✓ ምርት ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ በጥሬ ዕቃ እጥረት ምክንያት ከቆመ በኋላ የግዥ ጥያቄ የሚቅርብ መሆኑ፣
- ✓ የእጅ መብሻ ማሽኖች /Hand driling Machine/ ግማሾቹ በተለያየ ጊዜ ቢጠገኑም ተመልሰው ወደ ሥራ መግባት የማይችሉበት ደረጃ ላይ የደረሱ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ በተደጋጋሚ በመበላሸት የማምረት ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደሩ መሆኑን፣
- ✓ ድርጅቱ የፈጸማቸው የግዢ ውሎች አልፎ አልፎ ውሉ የተደረገበትን እና ውሉ የሚጠናቀቅበትን ጊዜ የሚገልጹ አለመሆኑ፣
- ✓ የድርጅቱ በጥቅል (bulk) መገዛት ያለባቸውን ዕቃዎች በቁጥ ቁጥ ግዢ በፕሮፎርማ የሚገዛ መሆኑ፣
- ✓ አንዳንድ ዕቃ አቅራቢዎች በግዥ ውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውል የገቡበትን ዕቃ ገቢ የማያደርጉ መሆኑን፣
- ✓ በድርጅቱ ተገዝተው መጋዘን ገቢ የሆኑ ዕቃና መሳሪያዎች አልፎ አልፎ በግዢ ትዕዛዙ (በስፔስፊኬሽኑ) መሰረት መሆናቸው በሚመለከተው አካል (ባለሙያ) የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- ✓ ወደ ድርጅቱ እቃ ግምጃ ቤት በተለያየ ምክንያት ተመላሽ የተደረጉ እቃዎች ተገቢው የገቢ ደረሰኝ የማይዘጋጅላቸው መሆኑ፣

- ✓ ተመላሽ የተደረጉ ጥሬ ዕቃዎች ገቢ ሳይደረጉና ሳይመዘገቡ ማስታወሻ እየተያዘ በሥራ ላይ የሚውሉ መሆኑ፣
- ✓ ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎችን ለማምረት፣ ለማሻሻልና ጥራታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል ጥናትና ምርምር አለማካሄዱ፣
- ✓ ድርጅቱ የመማርያና የማስተማሪያ መፃሐፍትን ልዩ ልዩ ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ ጽሑፎችን፣ ቻርቶችን፣ ካርታዎችንና ሥዕላዊ መግለጫዎችን እንዲሁም ለመዋለ ሕፃናት፣ ለሙዚቃ፣ ለሥነ ጥበብ እና ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አሰጣጥ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ አለማምረቱ፣
- ✓ ድርጅቱ በግዥ፣ በምርት ሂደትና በስርጭት ላይ ያሉትን ሠራተኞች ክህሎት በመደበኛ ትምህርትና በስልጠና ለማሣደግ በበቂ ሁኔታ እየሰራ አለመሆኑ፣
- ✓ ድርጅቱ ምርቶችን ከደንበኞች ጋር በተዋዋለበት ወቅት እና ጥራት እንዲሁም በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ ያልቻለባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው፣
- ✓ ድርጅቱ የህትመት ማሽኖችን በተለያዩ ቦታዎች መትከሉ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎችን የሚያንር እና በምርት ሥራ ላይ የሚውለው ጊዜ በምልልስ የሚያባክን መሆኑ፣
- ✓ ድርጅቱ ከትምህርት ዘርፎች ጋር ያለውን ግንኙነት በማስፋትና ቴክኒካዊ ድጋፎችን በማድረግ እና በሽያጭ ጣቢያዎች ያለውን የሽያጭ እንቅስቃሴ የተሻለ እንዲሆን የምርት አቅርቦትን በማሻሻልና በማስፋት ለሽያጭ እድገት አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ለሚሰጠው የአገልግሎት ግዥ ከደንበኞች ግብረ መልስ አለመቀበሉ፣
- ✓ ድርጅቱ ተሰብሳቢ ሂሳቡን በወቅቱ ለመሰብሰብ አለመቻሉ፣
- ✓ ድርጅቱ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች፣ በህትመት ውጤቶች፣ በሽያጭ ሰራተኞች፣ በባዛርና ኢግዚቢሽን ምርትና አገልግሎቱን ወጥ በሆነ መልኩ የማያስተዋውቅ መሆኑ፣
- ✓ ድርጅቱ የተሟላና ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት በድርጅቱ ውስጥ ካሉ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች እና ከውጪ ደንበኞች ጋር የቅርብ ግንኝነት በመፍጠር ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ አለማድረጉ፣

ታውቋል፡፡

128. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

129. የድርጅቱ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆን፣ ከሀገሪቱ የትምህርት ፍላጎት ጋር የተጣጣመ እና መሰረታዊ የትምህርት መስፋፋት ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እንዲሆን እና ድርጅቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖረው እገዛ እንዲያደርጉ የሚከተሉት የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡-

- ✓ የግዥ ክፍሉ ውጤታማ ስራ እንዲሰራና የግዥ ሥራው የተቀላጠፈ እንዲሆን በተጠናው የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሰረት የሚፈለገውን ችሎታ

ያሟላ የሰው ሀይል መቅጠርና በሥራ ላይ እንዲሰማራ ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የግዥ ክፍሉ የሰው ሀይሉን በአግባቡ በማደራጀት የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት የግዢ እቅድ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ተግባራዊ ማድረግና አፈፃፀሙ እንዲጨምር እና ድርጅቱ ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዲያገኝ መስራት ይኖርበታል፡፡

- ✓ በየአመቱ በክፍሉ ለሚያዘጋጀው እቅድና ለተገኘው ክንውን የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊኖረውና ከዚሁ በመነሳት የግዢ ስርዓቱን በመገምገም ፈጣን እንዲሆንና እንዲሻሻል ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ በድርጅቱ አለ የተባለውን የወረቀት ችግር ለመፍታት ከውጪ ሀገር የተለያዩ አቅራቢዎችን በማወዳደር ወረቀት እንዲገዛ ሊያደረግ እንዲሁም ሌሎች በሀገር ውስጥ ያሉ የወረቀት አቅራቢ ደርጅቶችን በማሳተፍ የወረቀት አቅርቦቱ እንዲጨምር ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ በድርጅቱ ያሉትን ያረጁ ማሽኖችን በአዲስ በመተካትና ጥገና በማካሄድ በሥራው ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን በመቅረፍ በነፃ ገበያው ውስጥ ለመሳተፍና ተወዳዳሪ ለመሆን መንቀሳቀስ ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ በየዕቃዎቹ አይነት በተለይ ጥሬ ዕቃን በተመለከተ አነስተኛና ከፍተኛ የክምችት መጠን ወስኖ ሊያዝና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ ጥሬ ዕቃ ከሚያቀርቡ አቅራቢዎች ጋር የሚያደርጋቸው የአገልግሎትም ሆነ የእቃ ግዢ ውሎች ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግባቸው፣ ተፈላጊውን መስፈርት፣ ውሉ የተደረገበት እና ውሉ የሚጠናቀቅበት ጊዜ በግልጽ ሊቀመጥ እንዲሁም አቅራቢዎች ውል የገቡለትን ዕቃ በውላቸው መሰረት በጊዜ ገደቡ እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ በጥናት ላይ ተመስርቶ አላስፈላጊ ክምችትን በማይፈጥር መልኩ ከወቅቱ ጋር በማገናዘብ ተፈላጊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን እና የመለዋወጫ ዕቃዎችን በጥቅል በመግዛት የቁጥቁጥ ግዥዎችን በማስወገድ አላስፈላጊ ወጪዎች መቀነስ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ለፈርኒቸር ምርት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ገበያ በሰፊው የሚገኙ በመሆኑ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ በተደጋጋሚ በፕሮፎርማና በውስን ጨረታ መግዛቱ ቀርቶ በግልጽ ጨረታ መግዛት አለበት፡፡

- ✓ በድርጅቱ ተገዝተው መጋዘን ገቢ የሚሆኑ ዕቃዎችና መሳሪያዎች በትዕዛዙ (በስፔስፊኬሽኑ) መሰረት መሆናቸው በቅድሚያ በሚመለከተው አካል (ባለሙያ) ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ ከውጭና ከሀገር ውስጥ ተገዝተው ለሚገቡ እና ሌሎች ንብረቶች የገቢ ደረሰኝ በማዘጋጀት እንዲመዘገቡ እና ለታቀደላቸው ሥራ እንዲውሉ ሊደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ በትምህርቱ ዘርፍ በጥራት ላይ ለሚያበረክተው አስተዋፅኦ እገዛ እንዲያደርግና የተሻለ ምርት አምርቶ ገበያ ማስፋት እንዲችል ለትምህርቱ ዘርፍ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችሉ ምርቶችን ሊያመርት ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ በግዥ፣ በምርት ሂደት እና በሽያጭ ላይ ያሉ ሰራተኞች ሥራቸውን በተገቢው ሁኔታ እንዲያከናውኑና ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ በዕቅድ የተመራና ወጥ የሆነ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ የሚያመርተውን ምርት በውሉ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብና በስፔስፊኬሽን መሰረት አምርቶ ለደንበኞች ሊያስረክብ ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ የሚያመርታቸው ምርቶች ወጪና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሆኑ በተለያዩ ቦታዎች የተተከሉ ማሽኖች አንድ ቦታ ተሰብስበው እንዲተከሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ድርጅቱ ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከሚመለከታቸው የትምህርት ዘርፎች፣ የግልና የመንግስት ድርጅቶች፣ ተቋማትና መ/ቤቶች ጋር የስራ ቅንጅትና የቴክኒክ ድጋፎችን በመለዋወጥ በጋራ መስራት እና ለሽያጭ ምርት እድገት አስተዋፅኦ ለማድረግ እንዲሁም የደንበኞችን ፍላጎት በማሰባሰብ የውጭ ግዥ አገልግሎቱን በማስፋት በተለይ በኬሚካልና በአፓራተስ ላይ ያለውን ፍላጎት በማሟላት የሚሰጠው የግዥ አገልግሎት የደንበኞችን ፍላጎት የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ እና ግብረ መልስ መቀበል አለበት፡፡
- ✓ በድርጅቱ በተሰብሳቢነት የሚታየው ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በአጭር ጊዜ ሊሰበሰብ የሚችልበትን ስልት በማዘጋጀት ትኩረት ሰጥቶት ሊሰራ ይገባል፡፡ በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙትን ተሰብሳቢ ሂሳቦች አፈፃፀም በመከታተል ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

- ✓ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን፣ አሰራሮችንና ዲዛይኖችን ወደ ድርጅቱ በማስገባት ከኋላ ቀር ሥራ ለመውጣት እንዲሁም ጥራት ያለውና ከጊዜው ጋር የሚሄድ የተሻሻለ ምርት በማምረት የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ጥናት በማካሄድ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ በየሽያጭ ጣቢያዎቹ ሽያጫቸው ዝቅተኛ የሆኑትን ዕቃዎች ከሌሎች ድርጅቶች መሸጫ ዋጋ ጋር በማነፃፀር እንዲሁም የማስተዋወቅ ሥራ በመስራት ሽያጩ እንዲጨምር ማድረግ፣ በአጠቃላይ ስለድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ ሰፋ ባለና ተደራሽ በሆነ መንገድ የማስተዋወቅ ሥራ ሊሰራ እንዲሁም ድርጅቱ ስለሚያመርተው ምርትና ስለሚሰጠው አገልግሎት የሚያደርጋቸውን የማስታወቂያ ሥራዎች ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡
- ✓ ድርጅቱ የተሟላና ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ፣ በድርጅቱ ውስጥ ካሉ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች እና ከውጪ ደንበኞች ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ስለምርቱ ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ የዋጋ ዝርዝር ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡

130. በመጨረሻም በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ዋና መ/ቤት፣ የሽሮሜዳ ቅርንጫፍ መ/ቤት እንዲሁም በናሙና የታዩት ባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1 ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ 2 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
1. በድርጅቱ የተፈፀሙት የትምህርት መሳሪያዎች ግዥዎች የመንግስትን የግዥ ሥርዓትን ተከትሎ የተፈፀሙ መሆኑን እና በወቅቱ ለተጠቃሚው ክፍል የተሰራጩ መሆኑን ማረጋገጥ፤	1. የግዢ ክፍሉ በሚገባ የተደራጀና ብቃት ባለው የሰው ኃይል የተሟላ ሊሆን ይገባል፡፡
	2. የግዥ ክፍሉ ከተጠቃሚ ክፍሎች የተሰበሰበውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ግልጽና ሊለካ የሚችል የግዥ መርሀ ግብር (እቅድ) በቅድሚያ ሊያዘጋጅና ሊተገበር ይገባል፡፡
	3. ግዥዎች መፈጸም ያለባቸው በቅድሚያ በተዘጋጀላቸው ዕቅድና በጀት መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡
	4. የግዥ ክፍሎች በየጊዜው ስለሚዘጋጀው የግዥ እቅድና ክንውን የተጠናከረ መረጃ መያዝና የግዢ ሥርዓቱን መገምገም እንዲሁም ፈጣን ማድረግ ይኖርበታል፡፡
1.1. የድርጅቱ የግዥ ሂደት የመንግስትን የግዥ ደንብ እና መመሪያ ተከትሎ ተፈፀመ መሆኑን መገምገም፣	5. የድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ በዕቃና በመሳሪያዎች አለመሟላት ምክንያት ምርት እንዳይስተጓጎል ሊደረግ ይገባል፡፡
	6. አላስፈላጊ ክምችት እንዳይያዝ በየዕቃዎቹ ዓይነት አነስተኛና ከፍተኛ የክምችት መጠን (minimum & maximum stock level) ሊወሰንና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
	7. ግዢ ከመፈቀዱ በፊት ለግዢ የተጠየቁ ዕቃዎች በግምጃ ቤት በሚፈለገው መጠንና ዓይነት አለመኖራቸው (out of stock) በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
	8. ድርጅቱ በተደጋጋሚ ዕቃ የሚያቀርብለትን ሻጭ የሥራ አፈፃፀም ሁኔታ በየጊዜው መገምገም አለበት፡፡
	9. የካፒታል በጀት ግዢ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መከናወን ይገባዋል፡፡
	10. የግዢ ውሎች ሲዘጋጁ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግና ለአገልግሎትም ሆነ ለእቃ ግዢ ተፈላጊው መስፈርትና ሊጠናቀቅ የሚችልበት ጊዜ በግልጽ ሊቀመጥ ይገባል፡፡
	11. የአቅራቢዎች ዝርዝር እና የአቅርቦት ታሪክ በአግባቡ እየተመዘገበ ሊያዝ ይገባል፡፡
	12. በግዥ ሂደቶች ላይ መጓተት እንዳይደርስ የግዢ ጥያቄዎች ግልጽና የማያሻማ (በአይነት፣ በብዛት፣ በጊዜ፣ በቦታና በተለያዩ መስፈርቶች) ተዘርዝረው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
	13. የጨረታ ግዥን የሚፈቅዱና የሚያጸድቁት በግዥ መመሪያ መሰረት ሥልጣኑ የተሰጣቸው ኃላፊዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡
	14. የጨረታ ሰነድ አቀባበልና አያያዝ ሚስጥራዊነቱን በጠበቀ ሁኔታ ኃላፊነት በተሰጠው ሠራተኛ ሊሆን ይገባል፡፡
	15. ጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ ሊቋቋምና ሥራውን በግዢ መመሪያው መሰረት በተቀመጡ መስፈርቶች የግዢ ዕቅድን ተከትሎ ሊሰራ ይገባል፡፡
	16. ድርጅቱ ግዥዎችን በጅምላ (bulk) መፈጸም አለበት፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
	17. ድርጅቱ የግዢ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች የሥራውን ይዘት እንዲያውቁት በማድረግ ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ማስቻል አለበት፡፡
1.2. በድርጅቱ የተፈፀሙ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥና ስርጭት በውሉ መሰረት መፈፀማቸውን በወቅቱ ለተጠቃሚው ክፍል መሰራጨታቸውን መገምገም፣	18. ዕቃ አቅራቢዎች በግዥ ውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውል የገቡለትን ዕቃ ገቢ ማድረግ አለባቸው፡፡
	19. ተገዝተው መጋዘን ገቢ የሚሆኑ ዕቃና መሳሪያዎች በትዕዛዙ (Specification) መሰረት ስለመገዛታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
	20. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር ግዢ በሚከናወንበት ወቅት ዕቃው ተገዝቶ ገቢ ስለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡
	21. ከግዢ ትእዛዝ ውጪ ለሚቀርቡ ዕቃዎች አቅራቢው ሊወስደው ስለሚገባ ኃላፊነትና ተጠያቂነት በግዥ ውሉ ውስጥ በተቀመጠው መሰረት ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
2. ድርጅቱ ለተጠቃሚው ሚፈልገውን ምርት በመጠን፣ በአይነትና በጥራት በሚፈለገው ጊዜ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያቀርብበት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን መገምገም፤	22. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎችን ለማምረት፣ ለማሻሻልና ጥራታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችል ጥናትና ምርምር ማካሄድ እንዲሁም አዳዲስ ዲዛይኖችንና አሠራሮችን በመዘርጋት ሥራ ላይ ማዋል አለበት፡፡
	23. ዕለታዊ የጥገናና የመሳሪያዎች የማምረት አቅም መከታተያ ቅፆች ማዘጋጀት አለባቸው፡፡
	24. የልማት ድርጅቱ የመማርያና የማስተማሪያ መፃሕፍትን ልዩ ልዩ ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ ጽሑፎችን፣ ቻርቶችን፣ ካርታዎችንና ሥዕላዊ መግለጫዎችን እንዲሁም ለመዋለ-ሕፃናት፣ ለሙዚቃ፣ ለሥነ ጥበብ እና ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አሰጣጥ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ሊያመርት ይገባል፡፡
	25. ድርጅቱ የሰው ኃይሉን በተለይ በግዢ፣ በምርት ሂደትና በስርጭት ላይ ያሉትን ሰራተኞች ክህሎት በመደበኛ ትምህርትና በስልጠና ማሣደግ አለበት፡፡
	26. ድርጅቱ የተመረቱ ምርቶች በተገባው ውለታ መሰረት በጥራትና በጊዜ ገደብ ለደንበኞች ማስረከብ አለበት፡፡
	27. ምርቶች በተገለፀው ስፔስፊኬሽን መሰረት ተመርተው ለደንበኞች መረከብ አለባቸው፡፡
	28. በሁለት የተለያዩ ቦታዎች ላይ የተተከሉ ማሽኖች የሥራ ፍሰታቸውን በመጠበቅ በአንድ ቦታ ተሰብስበው መተከል አለባቸው፡፡
	29. የግብዓት ማከማቻ መጋዘኖች በማምረቻው አጠገብ መሆን አለባቸው፡፡
3. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎች ግዢና ስርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር	30. ለደንበኞች በሚሰጠው የግዢ አገልግሎት ፍላጎታቸውን የሚያረካ መሆኑን ግብረ መልስ ማግኘት አለበት፡፡
	31. ድርጅቱ ከትምህርት ዘርፎች ጋር ግንኙነት በመፍጠርና ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት ለሽያጭ ምርት እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues)	የኦዲት መስፈርቶች (Evaluative Criteria)
ሥርዓትን የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን እና ቀልጣፋ ኢኮኖሚያዊ እና ብቃት ያለው የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን መገምገም፤ 3.1. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎች ግዢና ስርጭትን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓትን ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤	32. ድርጅቱ ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከሚመለከታቸው የግልና የመንግስት ድርጅቶች፣ ተቋማትና መ/ቤቶች ጋር የስራ ቅንጅትና የቴክኒክ ድጋፎችን በመለዋወጥ በጋራ መስራት ይኖርበታል።
	33. የደንበኛውን ፍላጎት በሚያረካ ሁኔታ በወቅቱና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሰብሰብ አለበት።
	34. ድርጅቱ ለሳይንስ ኪት አያያዝና አጠቃቀም ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ትምህርት ቢሮዎችና መምህራን መስጠት አለበት።
3.2. ድርጅቱ የትምህርት መሳሪያዎች ግዥና ስርጭት በተመለከተ ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊና ብቃት ያለው የመረጃ ልውውጥና ምርትን የማስተዋወቅ ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤	35. በተለያየ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ፣ በህትመት ውጤቶች፣ በሽያጭ ሰራተኞች፣ በባዛር፣ በኢግዚብሽንና በመሳሰሉት በመጠቀም ምርትና አገልግሎትን የማስተዋወቅ ሥራዎች ወጥ በሆነ መልኩ መከናወን አለባቸው።
	36. ድርጅቱ ለደንበኞች የተሰሩ ማስታወቂያዎችን ውጤት መገምገም አለበት።
	37. ድርጅቱ የተሟላና ጠንካራ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማለትም የመረጃ መረብን በመዘርጋትና በመጠቀም በድርጅቱ ውስጥ ካሉ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች እና ከውጪ ደንበኞች ጋር የቅርብ ግኑኝነት መፍጠር፣ ስለምርቱ ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ የዋጋ ዝርዝር፣ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ አለበት።
	38. ድርጅቱ በሥራ ሂደቱ እና በደንበኞች መካከል ያለውን ምልልስ ለመቀነስ እንድያስችል የደንበኞች አገልግሎት መርሀ ግብርመቅረፅና ተግባራዊ ማደረግ አለበት።

አባሪ 3 በናሙና የታዩ ትምህርት ቢሮዎች፣ ት/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ዝርዝር

ተ.ቁ	ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ት/ቢሮዎች	ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ት/ቤቶች	ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ዩኒቨርስቲዎች	መጠይቅ (Survey) የተበተነባቸው
1	ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ	ለዳግማዊ ሚኒሊክ የከፍተኛ ት/ት መሰናዶ ትምህርት ቤት	ለአዳማ ዩኒቨርስቲ	ለደ/ብርሃን ዩኒቨርስቲ
2	ለሲዳማ ዞን ትምህርት መምሪያ	ለሰላም ህፃናት መንደር ኮሌጅና ትምህርት ቤቶች	ለአዋሳ ዩኒቨርስቲ	ለዲላ ዩኒቨርስቲ
3	ለሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ	ለደጃች ወንድራድ /የመ/ደ/ትምህርት ቤት	ለአዲስ አአበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩንቨርስቲ	ለወሎ ዩኒቨርስቲ
4	ለኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ	በአዳማ ከተማ ለሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች		ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ
5	ለአዳማ ከተማ ትምህርት ቢሮ	በአሰላ ለሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች		ለሀሮማያ ዩኒቨርስቲ
6	ለአሰላ ከተማ ትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት	በሻሸመኔ ለሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች		ለወልድያ ዩኒቨርስቲ
7	ለባቱ ከተማ ትምህርት ፅ/ቤት	ዝዋይ ለሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች		ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ
8	ለሻሸመኔ ከተማ ትምህርት ፅ/ቤት	አዋሳ ለሚገኙ አራት ትምህርት ቤቶች		ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ት/ቢሮ
9	ለአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ			ለሀረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ
10	ለጉለሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት			ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
11	ለትምህርት ሚኒስቴር			ለሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ
12	ሀዋሳ ለሚገኘው ለድርጅቱ ሽያጭ ጣቢያ			ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ
13				ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ
14				ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ
15				ባህርዳር ለሚገኘው የድርጅቱ ሽያጭ ጣብያ

አባሪ 4፡ በአጠቃላይ በድርጅቱ ያሉ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

የድርጅቱ ሥም	ያልተሰበሰበው ሂሳብ መጠን (በብር)	ሂሳቡ የቆየበት ጊዜ	ያለበት ሁኔታ
ለኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ	41,544,526.20	ከ1991 እስከ 2005 ዓ.ም	ብር 10,040,126.28 በድርድር ለመክፈል
ትምህርት ሚኒስቴር	196,524.74	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	በድርጅቱ ክስ የተመሰረተ
ትምህርት ሚኒስቴር	4079176.62	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	
ለአሸናፊ መፃህፍት መሸጫና ማከፋፈያ ድርጅት	276,642.05	በ1999 እና በ2000 የተሰጠ ሲሆን እስከ 2006 ዓ.ም ያልተከፈለ	በድርጅቱ ክስ የተመሰረተና የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት
ከአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ	2,193,931.81	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	
ከአማራ ብ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ	3,943,838.55	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	
ከባህር ዳር ዩኒቨርስቲ	689,101.18	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	
ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ	231,192.36	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	
ከሀረር ብ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ	245,925.68	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	
ከትግራይ ብ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ	479,584	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	
ከሜጋ ማተሚያ ቤት	949,006.70	እስከ ሰኔ 30 2005 ዓ.ም	
ከሜጋ መፃህፍት መደብር	16694.83	ከ2001 እስከ 2005 ዓ.ም	
ከኤደን መፃህፍት መደብር	8636.85	ከ2002 እስከ 2005 ዓ.ም	
ከአፍሪካ መፃህፍት መደብር	10266.50	ከ2001 እስከ 2005 ዓ.ም	
ከዩኒቨርሳል መፃህፍት መደብር	18141.65	ከ2002 እስከ 2005 ዓ.ም	
	54,883,189.60		